



በደን ልማት ያጌጠችው ቤተ ክርስቲያን



በጎጃም ሀ/ስብከት የሚገኘው የወነባ ቅ/ሚካኤል ቤተክርስቲያን



www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ሥርዓትና ዜና ፡ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ።»


ዋና አዘጋጅ
ሊቀ ኅሩያን ልሣነ ወርቅ በዛብኀ
ም አዘጋጅ መ/ክንፈ
ርግብ ማርቆስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ በወር አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 110754
የመልእክት ሣ·ቁ· 3137
አዲስ አበባ ፡


## ማውጫ

**አርእስት** | **ገጽ**


ደብዳቤዎች ........ ፩
ርእሰ አንቀጽ ........ ፪
የልደት በዓል አከባበር ........ ፬
እግዚአብሔር ምስሉን ........ ፯
ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ በሰሜን ወሎ ........ ፲
በጠ ቤተ ክህነት አዲስ አስተዳዳሪ ተሾሙ ........ ፲፪
የደብረ ኃይል ራጉኤል የሰንበት ተማሪዎች ........ ፲፫
የሴቶች ዓምድ ........ ፲፬
በጎ አድራጊዎችን ርዳታ የሚጠይቁ ........ ፲፯
የአፈ መምህር ገበየሁ መንፈሳዊ ተግባር ........ ፲፯
ዜና ሊቃውንት ........ ፲፯
የአዲስ አበባ ሀ ስብከት ፩፻፶ ካህናትን አስመረቀ ........ ፲፱
የሊቀ ዲያቆን እሸቱ ሙሴ ታሪክ ........ ፳፩
ጤናችን ........ ፳፪
የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ........ ፳፫


# ደብዳቤዎች

ለክቡራን የትንሣኤ መጽሔት አዘጋጆች

ከሁሉ አስቀድሜ የእግዚአብሔር አብ ጸጋ የእግዚአብሔር ወልድ ቸርነት የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም አንድነት ከሁላችን ጋር እንዲሆን እመኛለሁ፡— ውድ አዘጋጆች ይሄውላችሁ ይህንን ደብዳቤ የጻፍኩላችሁ የመጋቢትና የሚያዝያ ወር ፲፱፻፹፪ ዓ·ም ትንሣኤ መጽሔትን ለመጀመሪያ ጊዜ አግኝቼ ሳነብ አድራሻችሁን በማግኘቴ ነው ።

እኔ ባለሁበት በወለጋ ሀ/ስብከት በግምቢ ከተማ ደብረ ፀሐይ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ት ቤት ከተጀመረ ዓመት ከመንፈቅ ሲሆነው ምንም መጽሔት አላገኘንም ለምን አትልኩልንም? ።

ሁለተኛ መጽሔቱን ለትምህርት ስለምንፈልገው በቀጥታ በአድራሻችን ትልኩልን ዘንድ በትሕትና እንጠይቃለን ።

ኃይለ ኢየሱስ ወ/ሀ/ስብከት ግንቢ ከተማ የሰ/ት/ቤት አባል የፓ/ሣ·ቁ ፸፪

<u>መልስ</u> ፡ ተማሪ ኃይለ ኢየሱስ በመጀመሪያ የምናቀርብልህ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መንፈሳዊ ሰላምታ ነው ቀጥለን ለጥያቄዎችህ መልስ እናቀርባለን ፡— ትንሣኤ መጽሔት ለምን አትልኩልንም ስላልከው ለወለጋ ሀ/ስብከት በየሁለት ወሩ ፩፻፱ ትንሣኤ መጽሔት በየወሩ ፵፰ ድምፅ ተዋሕዶ ጋዜጣ እየታተመ ይላካል ሀ/ስብከቱ በልዩ ልዩ ምክንያት ድርሻውን በወቅቱ እየወሰደ ማከፋፈል ሲናርበት ያዘገየዋል እንጂ ከእኛ ስሕተት አይደለም የማይደርሳችሁ በግል ተመዝግባችሁ የመጽሔቱን ዋጋ ካልከፈላችሁ በስተቀር እኛ ለመላክ አንችልም የምንልክላችሁ በሀ/ስብከቱ በኩል ነው ።

ለወደፊቱ በቀጥታ እንድንልክላችሁ ከፈለጋችሁ የመጽሔቱን ዋጋ ከእነ መላኪያው አስቀድማችሁ መክፈል አለባችሁ ።

፪ኛ/ ይድረስ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የትንሣኤ መጽሔት አዘጋጆች ከሁሉ አስቀድሜ በልዑል እግዚአብሔር ስም ሰላምታ እያቀርብኩ ወደሚከተለው ጥያቄ አመራለሁ በድምፀ ተዋሕዶ ጋዜጣ አንብቤ እንደተረዳሁት ሐኪም መለስ ማሞ የተለያዩ በሽተኞችን ያድናሉ ይባላል የእኔም ወላጅ እናት በማይድን በሽታ ተለክፋብኛለች ከተለያዩ ሐኪም ቤቶች ሂዳ ተመርምራ ነበር ከሕምሟ እንኳን ልትድን የበሽታውን ዓይነት እንኳን መርምሮ አውቆ የሚነግራት ሐኪም እስከ ዛሬ ድረስ አላገኘችም ። ስለዚህ በጋዜጣችሁ በተገለጸው መሠረት እናቴን ወስጄ ለማሳከም ከፍተኛ ጉጉት አድሮብኛልና የሐኪም መለሰ ማሞን አድራሻ እባካችሁ በትንሣኤ መጽሔት ገልጻችሁ ጻፉልኝ።

ተማሪ ፍጹም ካሣ
ምሥራቅ ሸዋ ናዝሬት

<u>መልስ</u> ፡ ተማሪ ፍጹም ስለ አቀረብክልን ሰላምታ እኛም በበኩላችን መንፈሳዊ ሰላምታ እናቀርብልሃለን — የሐኪም መለሰ ማሞን አድራሻ እንድንገልጽልህ ጠይቀሀል ቦታቸው በጽሑፍ ብቻ ተገልጾ የሚታወቅ አይደለም፡ ራስህ ቤተ ክህነት መጥተህ ከስብከተ ወንጌል መምሪ... ለመረዳት የምትችል መሆኑን እንገልጽልሃለን ።

፫/ ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ

አዲስ አበባ ፡

በመጀመሪያ የእግዚአብሔር ሰላምታየን እያቀርብኩላችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች አቀርባለሁ ።

፩ኛ/ የኢ/ኦ/ተ/ቤተ ክርስቲያን የሚያሳትማቸው ጋዜጦችም ሆኑ መጽሔቶች እኔ በምኖርበት አካባቢ በአርሲ ሀ/ ስብከት በጋለማ አውራጃ በበቆጂ ከተማ ለአንባብያን በቶሎ አይደርሱም የሚደርሱት ከታተሙ ፫ ወራት በኋላ ነው ችግሩ ለአርሲ ብቻ ነው? ወይስ ለሁሉም የሚደርሰው እንደኛው ዘግይቶ ነው? ችግሩስ ምንድን ነው?

፪ኛ/ በአሁኑ ወቅት መናፍቃን በየቦታው እንደአሸን በመፍላታቸው ሕዝበ ክርስቲያኑ ተገቢውን እርምጃ እየወሰደ ሳለ የቤተ ክህነቱ ኃላፊዎች መልካም ትብብር የማያሳዩ ለምንድ ነው?

፫/ ጴንጤዎችን አንዳንድ እስተማሪዎች መናፍቃን ይሏቸዋል ምን መባል እንደሚገባቸው በጽሑፍ ግለጹልን እባካችሁን?

፬/ ለአርሲ ሀ/ስብከት አርዓያ የሆነው የበቆጂ ከተማ መናፍቃንን የማጥፋት እንቅስቃሴ እያደረገ ነው ። እንቅስቂሴውንም የሚገልጽ ፲፯ ገጽ ጽሑፍ አዘጋጅቻለሁ ይህንን ጽሑፍ በየት በኩል ላቀርብ እችላለሁ?

አርሲ ሀ/ስብከት በቆጂ ደብረ ፀሐይ እስክንድር መርሐ ጽድቅ

መልስ፡—

እስክንድር መርሐ ጽድቅ ላቀረ

(ወደ ገጽ ፫ ዞሯል)



www.ethiopianorthodox.org

## ርእሰ አንቀጽ

# ወደ ሕዝቤ ማንን ልላክ?

ላኪና ተላኪ እንደሰጭና ተቀባይ ያሉ ናቸው ከአንድ ሀገር ወደ ሌላው ሀገር ከአንዱ ሰው ወደ ሌላው ሰው መላክ የተለመደ ተግባር ነው ፡ መልእክቱ ግን የተለያየ ሊሆን ይችላል የሰላም መልእክት አለ የጥፋትም አለ ።

እግዚአብሔር አምላክ በጥንተ ፍጥረት በመጀመሪያ የፈጠረው የሚላኩ መላእክትን ነው እነርሱም የሚላኩት በእርሱ ፈቃድ ስለሆነ ለምሕረትም ለመዓትም ለሰላምም ለጥፋትም ይላካሉ ፈጣሪያችን ቸርነቱንም ሆነ መዓቱን ወደ ሰዎች የሚልከው በመላእክት አማካይነት እንደሆነ ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዱናል ። ሐዋርያው ጳውሎስ ለሮሚ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ (ምዕ ፱·፳፪) እግዚአብሔር ኃይሉን የሚገልጽበትን ቁጣቱን ሊያሳይ ቢወድ ትዕግሥቱን ካሳየ በኋላ ለማጥፋት የተዘጋጁትን ቁጣውን የሚገልጽበት መላእክትን ያመጣል ፡ ዳግመኛም የጌትነቱን ብዛት ሊያሳይ ቢወድ አስቀድሞ መርጦ በወደዳቸው ለይቅርታ የተዘጋጁ የይቅርታ መላእክትን ያመጣል” ይላል እግዚአብሔር አምላካችን አስቀድሞ ሳያስተምርና ሳያስጠነቅቅ በመከራ አይቀጣም በቀድሞ ዘመን የሰው ልጆች ሲበድሉ ከክፋታቸው እንዲመለሱ የሚመክሩና የሚያስተምሩ የሚገሥፁም ነቢያትን ካህናትን እያስነሣ በመምህርነት ይልክ ነበር ።

በዘመነ አበው ማስተማሪያና መማሪያ የሚሆኑ መጻሕፍት ባለመጻፋቸው ሰዎች የሚመሩት በሕገ ልቡና ብቻ ነበረ ሕገ ልቡናም ማለት የተፈጥሮ ዕውቀት ነው ። ሰው ባይማርም እንኳን የተፈጥሮ ዕውቀት ስላለው ክፋውንና መልካሙን ለይቶ የሚያውቅበት አዕምሮ አለው ።

ለምሳሌ በኖኅ ዘመን መጻሕፍት አልተጻፉም ነበር ።

ነገር ግን ኖኅ ጽድቅንና ኃጢአትን ለይቶ ዓውቆ በዘመኑ የነበሩ ሰዎች የሚሠሩት ሥራ ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላ መሆኑን አስረዳቸው ከስሕተታቸውም እንዲመለሱ መላልሶ ይመክራቸውና ያስተምራቸው ነበር እነርሱ ግን በተፈጥሮ በአገኙት ዕውቀት ካለመጠቀማቸውም ሌላ በኖኅ ምክርም አልተጠቀሙም ከዚህም ዕኩይ ተግባራቸው የተነሣ በማየ አይኅ ተደመሰሱ በተፈጥሮ ዕውቀቱ ተጠቅሞ ከክፉ ሥራ የተጠበቀው ኖኅ ግን ከእነርሱ ተለይቶ ከእነቤተሰቡ ከጥፋት ለመዳን ችሏል “አንተ ቤተሰቦችህን ይዘህ ወደ መርከብ ግባ ከዚህ ትውልድ በፊት ጻድቅ ሆነህ አይቼሃለሁና” ሲል እግዚአብሔር አምላክ መስክሮለታል ዘፍ·፯·፩

ከዚያም በኋላ በዘመነ መሳፍንትና በዘመነ ነገሥት ነቢያትን እያሥነሣ የሚሳሳተውን ሕዝብ እንዲመክሩና እንዲያስተምሩ ያደርግ ነበር ። ከልደተ ክርስቶስ በፊት በሰባት መቶ ዓ·ዓ ተነሥቶ የነበረው ነቢዩ ኢሳይያስ በሚያስተምርበት ዘመን ዖዝያን የተባለ ንጉሥ ነግሦ ነበር ሊቀ ካህናቱም አዛርያስ ይባል ነበር ንጉሡ ለፍርድ ሲቀመጥ ነቢዩ በቀኙ ይቀመጣል ምነው በቀኜ ትቀመጣለህ? ይለዋል ካህን በንጉሥ በስተቀኝ ይቀመጥ ይልብሃል ይለዋል ፡ ከንጉሡ የበለጠ ልብስ ይለብሳል ምነው ከእኔ የበለጠ ልብስ ትለብሳለህ? ሲለው ካህናት የበለጠና የአማረ ልብስ ይልበሱ ተብሎ ተጽፏል ይለዋል መዝ ፩፻፴፩·፱ እንዲሁም የፈረደውን ፍርድ ይሽርበታል ምነው ፍርዴን ትገሥብኛለህ? ባለው ጊዜ ከመንግሥት ሥልጣን የክህነት ሥልጣን ይበልጣል ይልብሃል በማለት ቤተ መንግሥትን እያረካከሰ ቤተ ክህነትን እያሞገገሠ ስላስቸገረው ተበሳጨና ከቤተ መንግሥት ቤተ ክህነት የሚበልጥ ከሆነማ እኔስ ከአባቴ ከቤተ መንግሥት ብወለድ በእናቴ ከቤተ ክህነት እወለድ የለምን አለና ልብሰ ተክህኖ ለብሶ ማዕጠንተ ወርቁን ይዞ ሊያጥን ገባ ጢስ ቀታሬው ቢነካው በግንባሩ ላይ ለምፅ ወጣበት በሻሽ ሸፈነው ከሻሹ ላይ ወጣ በእስራኤላውያን ሕግ ለምፅ ያለው ሰው እንደርኩስ ስለሚቆጠር እርሱን አሥረው በእርሱ ፈንታ ልጁን አነገሠዋል ነገር ግን ይህ ሁሉ ስሕተት ሲፈጸም በዘመኑ የነበረው ነቢዩ ኢሳይያስ ባለማስተማሩ ከእግዚአብሔር ተሰጥቶት የነበረው ሀብተ ትንቢት ተነሥቶት ከከንፈሩ ላይም ለምፅ ወጥቶበት ሦስት ዓመታት ኑሯል ።

ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር አምላክ ያድነው ዘንድ ፈቃዱ ስለሆነ ወገኖቹ እስራኤል ኃጢአትን አብዝተው ሠሩ ጣዖትም አመለኩ ከኃጢአት ወደ ጽድቅ ከአምልኮተ ጣዖት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር እንዲመለሱ የሚያስተምር ማንን ልላክ? ሲል ተናገረ በዚህ ጊዜ ነቢዩ ኢሳይያስ ሀብተ ትንቢት ተነሥቶኛል ለምፅም በከንፈሬ ላይ ወጥቶብኛል እንጂ እኔ ሂጄ ለማስተማር ፈቃደኛ ነበርኩኝ በማለት ለመላክ ያለውን ፈቃድ ገለጸ ወዲያው ከለምፁ ይፈውስ ዘንድ ከሱራፌል አንዱን መልአክ ላከለት መልአኩም በጉጠት የእሳት ፍሕም ወስዶ ከንፈሩን ቢያስነካው ወጥቶበት የነበረው ለምፅ ጠፋለት ተነሥቶት የነበረውም ሀብተ ትንቢት ተመለሰለት እንደቀድሞው በንቃትና በትጋት በማስተማሩ ሕዝቡ ከስሕተት ሊመለስ ችሏል ።

ይህንንም ራሱ ኢሳይያስ ሲገልጽ “ከሱራፌልም አንዱ እየበረረ ወደ እኔ መጣ በእጁም ከመሠዊያው በጉጠት የወሰደው ፍሕም ነበር አፌንም ዳሰሰበትና እነሆ ይህ ከንፈሮችህን ነክቷል በደልህም ከአንተ ተወገደ፡ ኃጢአትህም ተሠረየልህ አለኝ የጌታንም ድምፅ ማንን እልካለሁ? ማንስ ይሄድልኛል? ሲል ሰማሁ እኔም እነሆኝ እኔን ላከኝ አልሁ እርሱም ሂድ ይህን ሕዝብ መስማትን ትሰማላችሁ አታስተውሉም ማየትም ታያላችሁ አትመለከቱም በላቸው በዓይናቸው እንዳያዩ በጆሮአቸውም እንዳይሰሙ በልባቸውም እንዳያስተውሉ ተመልሰውም እንዳይፈወሱ የዚህን ሕዝብ ልብ አደንድን ጆሮአቸውንም አደንቁር ዓይናቸውንም ጨፍን አለኝ” በማለት ተናግሯል ትን·ኢሳ· ፮·፮ — ፲ እግዚአብሔር አምላክ የነበረው በእነኢሳይያስ ዘመን ብቻ አይደለም ከዚያ በፊትም ነበረ ዛሬም አለ ወደፊትም ዓለምን አሳልፎ ለዘለዓለም ይኖራል በየጊዜው ለሚነሣው ትውልድ አስተማሪዎችን መካሪዎችን እየመረጠ ለመላክ ይፈልጋል ።

አሁንም በዘመናችን መምህር አጥተው ወደተጉዱ ወገኖቹ ማንን ልላክ? ይላል እንደነቢዩ ኢሳይያስ እኛ ለመላክ ፈቃደኞች ነን እኛን ላከን የሚሉ መልእክተኞች በብዛት እንዲቀርቡ ያስፈልጋል ። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠሩ ብዙዎች ናቸው የተመረጡ ግን ጥቂቶች ናቸው ብሎ እንዳስተማረን እንዲያስተምሩ የሚመደቡ ብዙዎች ሲሆኑ ለማስተማር በፈቃደኝነት የተሰለፉ ግን በጣም ጥቂቶች ሆነው እናገኛቸዋለን ።

በአሁኑ ጊዜ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ስለ እውነት የሚያስተምሩ ስለ እውነት የሚመሰክሩ ስለ እውነት የሚመክሩ መምህራንን ትፈልጋለች እንደነቢዩ ኢሳይያስ እኔን ላኩኝ እኔ እላካለሁ እያሉ በመቅረብ እውነተኛውን የእግዚአብሔርን ቃል ለማስተላለፍ የተዘጋጁ መምህራን የሚፈለጉት ነገ ከነገ ወዲያ ሳይሆን ዛሬ ነው ።

ቤተ ክርስቲያናችን የምታስተላልፈውን መመሪያ ተቀብሎ የማያስተምርና የማይመክር ቢኖር እንደ ነቢዩ ኢሳይያስ ለምፅ ወጥቶበት ሀብተ መንፈስ ቅደስ ተነሥቶት በሀፍረት ላይ ይወድቃል ።



## ደብዳቤዎች

(ከገጽ ፩ የዞረ)

ብካቸው ጥያቄዎች መልስ ከመስጠታችን አስቀድመን የበኩላችን የሰላምታ መልስ እናቀርባለን፡–

የሚታተሙት መጽሔቶችና ጋዜጦች በቶሎ አይደርሱም ስለምትለው በአሁኑ ጊዜ የወረቀት ችግር እንዳለ የተሠወረ አይደለም በችግር ምክንያት ዘግይቶ ሊታተም ይችላል ቢሆንም በተለይ በትንሣኤ መጽሔትና ድምፀ ተዋሕዶ ጋዜጣ የሚታተሙት ጽሑፎች ትምህርት አዘል በመሆናቸው እንኳን እስከ ሦስት ወር እስከዓመትም ቢቆዩ የሚሰለቹ አይደሉም በደረሱ ጊዜ አንብቦ ለመጠቀም ይቻላልና ።

ሕዝበ ክርስቲያኑ ስለ ሃይማኖታቸው አስፈላጊውን እርምጃ ሲያደርጉ የቤተ ክህነት ኃላፊዎች ትብብር የማያደርጉ ከሆኑ ወደ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ማሳሰቢያ አቅርቦ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወስድ ለማድረግ ይቻላል ።

ጴንጤዎች ምን መባል አለባችው ስለምትለው ከኦርቶዶክስ እምነት የተለዩ አማላጅነትን የማያምኑ በመሆናቸው ለግብራቸው የሚስማማ መስሎ የሚታየው በአንደኛ ደረጃ ጸረ ማርያም በሁለተኛ ደግሞ መናፍቃን መባል አለባቸው እንጂ ጴንጤዎች መባል አይገባቸውም በአራተኛው ጥያቄህ ላይ ልዩ ልዩ የሃይማኖት ድርጅቶችን የሚቃወም ጽሑፍ ማዘጋጀትህን ገልጸሕ በምን በኩል እንደምታቀርበው ጠይቀሃል በስብከተ ወንጌል መምሪያ በኩል ብታቀርበው መልካም ይመስለናል አፋጣኝ መልስ ለማግኘት የምትችለው በዚሁ መምሪያ በኩል ነውና ።



www.ethiopianorthodox.org

# የልደት በዓል አከባበር

ከንቡረ ዕድ አባ ኤዎስጣቴዎስ

በዓለ ልደት ቀደም ብላ በተጠናከረችው ቤተ ክርስቲያን መከበር የጀመረው በ፩፻፴፯ ዓ/ም ላይ እንደኾነ ታውቆአል ሆኖም ይከበር የነበረው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንደ አሳሰቡት ከዓመቱ በማናቸውም አመች ዕለት ነበር እንጂ ከጊዜ በኋላ እንደሆነው የተወሰነ ዓመታዊ ዕለት አልነበረውም የተወሰነ ዕለት ወርኅ እንዲኖረው የተደረገው በ፫፻፶፯ ዓ/ም ላይ ነው ። ይኸውም እንደዚያን ጊዜ አቆጣጠር ይዘታቸው ታኅሣሥ ፳፭ ነበር የሚከበረው ይህንም መጽሐፈ ፍትሐ ነገሥት በአንቀጸ ጾም ላይ ይጠቁማል (አንቀጽ ፲፭) ።

እንዲህም ከሆነ ዘንድ ብሔራዊት ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችንም በአንጻሩ እንደራስዋና እንደመሰልዎችዋ አብያተ ክርስቲያናት አቆጣጠር በመውሰድ ታኅሣሥ ፳፱ እንዲከበር አደረገች በብሔራችን የክርስቶስ በዓለ ልደት መከበር የተጀመረው በአራተኛው ምዕት ዓ/ም በአባ ሰላማ ጊዜ ነው ። እንግዲህ የመጀመሪያው አያያዝ ከላይ እንደተጠቀሰው በዓለ ልደት በቤተ ክርስቲያናችን እንዲከበር የተወሰነው ከታኅሣሥ ወር በሃያ ዘጠነኛው ዕለተ ወርኅ ብቻ ነበር ማለት ነው በዚህ ድንጋጌ መሠረት በዓለ ልደት እንደሌላዎቹ በዓላታ ሁሉ የአለ ምንም ለውጥ በቤተ ክርስቲያናችን ለብዙ ዘመናት ሲከበር የቆየው በዚህ ሁኔታ ነበር ። ይህም በሌላዎቹ በዓላት አከባበር በኩል የአለንን ትክክለኛ ይዘት ሊያረጋግጥልን ይችላል እንግዲያ የክርስቶስ በዓለ ልደት ከሌላዎቹ በዓላት ሁሉ ተለይቶና በዘመነ ዮሐንስ አንድ ዕለት ወደ ኋላ በመመለስ ተለውጦ ሊከበር የቻለው ለምንድን ነው? ቢባል መልሱ ሩቅ አይደለም ጌታችን ኢየሱስ ክርስ



ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በበረት እንደተወለደ

ቶስ የተፀነሰው በዘመነ ዮሐንስ መጋቢት ፳፱ ሲሆን የተወለደው እንደ መጀመሪያው ሥርዓተ ይዘት ዕለተ ክብር በዘመነ ማቴዎስ ታኅሣሥ ፳፱ እንደሆነ በአቆጣጠራችን የተረጋገጠ ነው እንግዲህ በሦስቱ ወንጌላውያን በዘመነ ዮሐንስ ፡ በዘመነ ማቴዎስና በዘመነ ማርቆስ መዋዕለ ፅንሱ ትርፍ ዕለት ሳይኖር እነዚያኑ የታወቁትንና በቁጥር የተወሰኑትን ፱ ወር ከ፭ ዕለታት ብቻ ይዞ ስለሚገኝ ያው እንደሥርዓቱ በታኅሣሥ ፳፱ እንዲከበር ሆነ ትክክልም ነው በዘመነ ሉቃስ ግን ዕለተ ሠግር (መጠነ ራብዒት) ስትጨመር ወደ ስድስተኛ ቁጥር በማውጣት ፱ ወር ከ፮ ዕለታት ልታደርገው የምትችል መስሎ ስለታየ ከወሩ ወደ ፳፰ኛው ዕለት እንዲመለስ የተደረገበት ምክንያት ይህ ነው ።

ይህ የተደረገበት ወቅት ከ፭፻፳፯ — ፭፻፷፭ በአለው ጊዜ ውስጥ በዮስጥንያኖስ ዘመነ መንግሥት እንደሆነ ታውቆአል ዮስጥንያኖስ በቁስጥንጥንያ ፴ ዓመታት የነገሠ ንጉሥ ነበረ ከቴዎዶስዮስ በኋላ የሮማ መንግሥት በምሥራቅና በምዕራብ ከሁለት ተከፍሎ ስለነበር ዮስጥንያኖስ የምሥራቁ ክፍለ መንግሥት (የቁስጥንጥንያ) መሪ ነበረ ማለት ነው ግብጽ ኢየሩሳሌምና (ከነዓን) ሦርያም በግዛቱ ውስጥ ነበሩ ዮስጥንያኖስ በእምነቱ የኬልቄዶንን ጉባዔ ቀኖና ተከታይ በመሆኑ ከዲዮስቆርስ እምነት ተከታዮች በቀር በጊዜው ከእምነቱ ውጪ የሆኑትን ሁሉ በማሳደድ ይፈጽመው የነበረው ደባ (ጌድራ) ቀላል አልነበረም የዲዮስቆሮስን (የኦርቶዶክስ) እምነት ተከታዮች የአልታወቀበት ምክንያት ደግሞ ባለቤቱ ስመ ጥርዋ ንግሥት ታእድራ የዲዮስቆሮስን እምነት (ተዋሕዶ ባሕርያት) ተከታይ ስለ ነበረች እርስዋን ለአለማስቀየም (ለማስደሰት) እንደነበር በታሪክ ታውቆአል ፤

በመሆኑም በዘመኑ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታዮች አባላት ከመለካውያን ተጽዕኖ ዕረፍት አግኝተው ሥርዓተ እምነታቸውን በመጠበቅ በደስታ ይኖሩ ነበር ወቅቱም በዐለ ልደት በዘመነ ዮሐንስ መቼ ዕለት መከበር እንደሚገባው የቤተ ክርስቲያን ሰዎች የሚጠያየቁበት ጊዜ ስለነበር በጊዜው የነበሩ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት አጋጣሚውን ተጠቅመው በመወያየት ልደት በዘመነ ዮሐንስ ከወሩ (ታኅሣሥ) በ፳፰ እንዲከበር በማድረግ ወስነው መታሰቢያነቱ ለንጉሥ ዮስጥንያኖስና ለንግሥት ታእድራ እንዲሆን እንደአደረጉ በአንድ አንድ የታሪክ ሊቃውንት ይነገራል ። እስከዚህ ጊዜ ድረስ ይከበር የነበረው ግን መሠረታዊ ዕለቱን ጠብቆ በ፳፱ ታኅሣሥ እንደነበረ ታውቆአል ይህም አድራጎት ዩልዮስ (ጁሴስ) ቄሣር ወርኀ ሐምሌን አውግስጦስ ቄሣር ወርኀ ነሐሴን እየበኩላቸው አንድ አንድ ዕለት እየጨመሩ በእየስማቸው እንደሰየሙ ድርጊቱ ይህን ይምሰል እንጂ ልክ ነበር ማለት አይደለም ፤ አስተሳሰቡ ጥራት በሌለው ድንገተኛ አመለካከት የተደረገ ነበር ይህንም ከሁኔታው ለማረጋገጥ ይቻላል ምክንያቱም ዕለተ ሰግር ማለትም ስድስተኛዋ ጳጉሜን ከዕለታት ውስጥ ገብታ የማትቆጠር በመሆንዋ ነው እንዴት (ለምን?) ቢባል ከአራቱም አዕዋደ ዓመታት (ዙር ዓመታት) ከሰዓት ተጠራቅማ ወደ ዕለት በመደመር የተገኘች ውጤት እንጂ ለእያንዳንዱ ወንጌላዊ (ዘመነ ኪሩብ) በዕለት የሚቆጠር ድርሻ ስለሌላት ነው ።

(ስድስተኛው ጳጉሜን ዕለተ ሰግር ሰግረ ዮሐንስ መጠነ ራብዒት) ቢል ትርጉሙ አንድ ነው ። (ዘመናቱ ከአራት ተከፍለው እንዲመደቡ የአደረገውም ቅሉ ይህ የተፈጥሮ ቀመረ ዕለት ወሰን ነው አዎ ዑደተ ፀሐይ በምልዐ ዕለት ዓመታቱን ለመሙላት የአለው ወሰን ፩ሺ፬፻፷፩ ቀመር ነው አብራርቶ ለማስቀመጥ ያህል የአንዱ ዙር ዓመት የዕለታት ቁጥር ፫፻፷፭·፮) ዕለት (ሦስት መቶ ስድሳ አምስት ዕለት ከስድስት ሰዓት) ፲፭ ኬክሮስ እንደሆነ እናውቃለን ። ስለሆነም የአራቱንም ክፍለ ዘመናት የዕለታት ቁጥር በዚህ መጠን በመውሰድ ስናባዛው ፫፻፷፭·፮ × ፬ = ፩ሺ፬፻፷፩ (አንድ ሺህ አራት መቶ ስድሳ አንድ) ዕለታት ይሆናል መልሰው ቢያካፍሉት ፩ሺ፬፻፷፩ ÷ ፬ = ፫፻፷፭·፮ ማለት ተመልሶ ያው ሦስት መቶ ስድሳ አምስት ዕለታት ከስድስት ሰዓታት በመሆን ያልቃል ማለት ነው እንግዲህ ከዚህ ላይ ትርፍ ሰዓት እንጂ ትርፍ ዕለት እንዳለ እንመለከትም አባቶቻችን መምህራን ዐውደ ፀሐይ የአንዱን ዘመነ ኪሩብ (ወንጌላዊ) ብቻ ይዞ ቢቆጥሩት ፫፻፷፭ ዕለታት ከ፲፭ ኬክሮስ እንደሆነ በማለበም የአስተማሩንም ስለዚህ ነው ከዚህ ላይ ከስድስት ካልዒት የሚለውን ተጨማሪ ቀመር የአለፍኩት በቃል ቢነገርም ዕጅግ በጣም አነስተኛ ከሆነ ዘንድ በዑደተ ፀሐይ ላይ ለውጥን (መፋለስን) የሚያስከትል ሆኖ ባለማግኘቱና እንደ ፲፭ቱ ኬክሮስ (ራብዕተ ዕለት) በግብር ተገልጦ በአገልግሎት ላይ የአልዋለ በመሆኑ እንጂ መምህራን ጨምረው የአስተማሩን መሆኑን በመዘንጋት አይደለም ።

አዎ (አንድ ነገር ለተጨባጭ ሁኔታ አመች ሆኖ እስከአልተገኘ ድረስ ትርፉን ትቶ ጐደሎውን መልቶ መናገር የተለመደ ነው በአቡሻክር (አቡሻከር) ትምህርት ስድስተኛው ጳጉሜን ከዓበቅቴ ገብቶ አይቈጠርም የተባለውም ስለዚህ ነው ። እርግጥ ነው በአራት አመታት ውስጥ ከእየዘመኑ የተገኘ እንደ መሆኑ መጠን አራቱም ዘመናት በሰዓት ሲሆን ፮—፮ በኬክሮስ ሲሆን ፲፭—፲፭ ድርሻ በማግኘት አድቅቀው (ተተናት ነው) ከተከፋፈሉት ዘንድ ዕለት ስለማይገኝ በዕለተ ቀመር በአበቅቴ ገብቶ አለመቀጠሩ ስለዚህ ነው ።

እንዲህም ከሆነ በመዋዕለ ጽንሱ ውስጥ ትርፍ ዕለት ሳይኖር እንደ አለ አድርጎ (አስመስሎ) በመቆጠር በዓለ ልደትን ከመደበኛ ቦታው (፳፱·፬) አንስቶ ወደ ፳፰·፬ እንዲለወጥ ማድረግ ትክ





www.ethiopianorthodox.org

ክል አይደለም በዚያውስ ላይ የሚ
ሆን ከሆነ የዕለተ ግዝረቱ (ጥር ፮)
የበዐተ ቤተ መቅደሱ (የካቲት
፰/የተሰብእቱ መጋቢት ፳፱) የመ
ታሰቢያ በዓላቱ በዚያው አንፃር
ወደ ኋላ እንዲሸጋሸጉ ለምን አል
ተደረገም? ይህ ብቻ አይደለም
መጠነ ራብዒት (፯ኛው ጳጉሜን)
ከዕለታት ገብቶ በዕለት በመቆ
ጠር በዓላትን ከእየቦታቸው የሚ
ያፋልስ ከሆነማ በዚሁ አንፃር
በአጋጣሚው ጊዜ ሁሉ የዓመቱን
በዓላት በሙሉ ወደ ኋላ ማሸጋሸግ
ግድ አይሆንምን? ነገር ግን ትክ
ክል በአለመሆኑ አላዛለቀምና በስ
ድስተኛው ጳጉሜን ምክንያት
ከዚህ ከክርስቶስ በዓለ ልደት
በቀር በማንኛውም ቢሆን ለውጥ
ተደርጎ አልታየም ለምሳሌ ፤ የአ
ቡነ ተክለ ሃይማኖትን ክብረ
በዐለ ልደት ብንወስድ ምንጊዜም
ቢሆን ያው የተለመደው ዕለት
(ታኅሣሥ ፳፬ እንደ ተጠበቀ ይኖ
ራል እንጂ አልተለወጠም በዚ
ህም ብቻ እንኳ ትክክሉ የትኛው
እንደሆነ ለማወቅ እንችላለን ይህ
ብቻ አይደለም ማንም ሰው እንደ
አጋጣሚ ሆኖ በስድስተኛ ዕለተ
ጳጉሜን ቢወለድ ወይም ቢሞት
የልደቱም ሆነ የሞቱ መታሰቢያ
ዕለት በመሆን ሊቆጠር የሚገባው
አልፎ በመስከረም ፩ ዕለት (ቀን)
እንጂ አራተኛውን ዓመት ጠብቆ
በስድስተኛው ዕለት ጳጉሜን
መሆን የለበትም ሊሆንም አይች
ልም እንዲሆንም ከሆነ በዓለ ልደ
ትን ከመደበኛ ቦታው (፳፱·፬)
ማታወስ ኢርቱዕ ይሆናል ።
ማለት ነው የበዓለ ልደትዕለተ
ክብር መለወጥ ከዚህም በቀር ሌላ
ችግር አስከትሉአል ይኸውም
በዓለ ልደት በ፳፰ ተከብሮ ሳኒ
ታው (፳፱) ረቡዕ ወይም ዓርብ

ዕለት ገጥሞ በዋለ ጊዜ "ይጾ
ማል" የለም አይጾምም ወይም
ይበላል የለም አይበላም የሚለው
አከራካሪ ጉዳይ ነው ይህም ነገር
ከሆነ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ
እውነቱ እንዲከሠት በማድረግ
ገና መፍትሔ ስለ አልተገኘለት
እንዲቱን ቤተ ክርስቲያን እየአለ
ያየ ይገኛል ። አሁንም እንኳ
በአጋጣሚው ጊዜ በአንዲቱ ሰበካ
ብሉት ነው ተብሎ ሲበላ በሌላ
ይቱ ጾም ነው ተብሎ ይጾማል
በአንዲቱ ሰበካ ጥዋት ሲቀደስ
በሌላይቱ ውሎ ይቀደሳል ከአን
ዲቱ ሰበካ ቤተ ክርስቲያን አባላት
እንኳ አንዱ ሲጾም አንዱ ይበላል
እንዲያውም አንዳንዶቹ ሰበካዊት
ቤተ ክርስቲያንና አንዳንዶቹ
ሊቃውንትስ እንደ ጥንታዊው
ሥርዓተ ይዘት በ፳፱ ብቻ በማክ
በር ከመጠቀም በቀር በ፳፰ የሚለ
ውን ለውጥ እስከ አሁን ድረስ
አልተቀበሉትም አንዳንዶቹ
ደግሞ በአንዳንድ ተጽዕኖ ምክን
ያት በ፳፰ ለማክበር ቢገደዱም
ትክክለኛ አለመሆኑን ኅሊናቸው
ስለአመነበት ልደት በ፳፱·፬
የሚል ድምፅ ደወል እየአሰሙ
ይገኛሉ ።

የበዓለ ልደት ዕለተ ክብር መለ
ወጥ ያስከተለው ችግር ይህ ብቻ
አይደለም በጾመ አብርሃም አጀማ
መር ላይም ተመሳሳይ ለውጥንና
ክርክርን አስከትሎአል አንዱ ግለ
ሰብእ ወይም አንዲቱ ሰበካ በመጽ
ሐፈ ፍትሐ ነገሥት በመመራት
መንፈቀ ኅዳርን (፲፮) በመያዝ
ስትጀምር ሌላው ግለሰብእ ወይም
ሌላይቱ ሰበካ "ሚናስ" በማለት
በኅዳር ፲፭ ትጀምራለች ይህውም
በዓለ ልደት ወይም ፳፰·፬ ከተለ
ወጠ ዘንድ የጾሙን ቁጥር ለማስተ
ካከል በማሰብ የተወሰደ ፈሊጥ

ነው ። ሌላዎቹ አንድ አንድ ኦርቶ
ዶክሳውያት አብያተ ክርስቲያ
ናት ደግሞ ጾመ አብርሃምን
ትተው በኅዳር ፲፱ በመጀመርና
ጾመ ስብከትን ብቻ በመጠበቅ
እንደሚጠቀሙ ይታወቃል ስንክ
ሣር ፲፱ ተመልከት የሚያስገር
መው ደግሞ ጉባዔ ሠርቶ ትክክለ
ኛውን ነገር አጥንቶ ቤተ ክርስቲ
ያኒቱን ለማስተባበር የአለመቻሉ
ጉድለት አንሶ ባህሉ እንደ ሕፀፀ
ሃይማኖት እየተቆጠረ አንዱ ሌላ
ውን መናፍቅ በማድረግ ለረዥም
ዘመናት እስበስ በመወነጃጀል
መኖሩን ነው በአንድ ብሔር ክል
ልና በአንድ ኤጲስ ቆጶስ ሥልጣን
ሥር የምትኖረው አንዲቱ ቤተ
ክርስቲያናችን ተዋህዶ ፤ ቅባት ፤
ጸጋ እየተባባለች በመለያየት ስት
ነቃቀፍ መኖርዋ እጅግ የሚያሳ
ዝን ነበር ቀድሞ ይህን ቅራኔ
አስወግዶ ቤተ ክርስቲያኒቱ በአ
ንድ ስያሜ (ኦርቶዶክስ ተዋህዶ)
ጸንታ በአንድ ቀመረ ባህልና ሥር
ዓት ተባብራ ለመኖር ከአላስቻል
ዋት ምክንያቶች አንዱና ዋናው
የጳጳሳቱ ባዕድነት እንደነበር ይነገ
ራል ። የመንግሥት ባለሥልጣና
ትም የአንዱን ወገን ለማጽደቅ
ሲሉ በአንዱ ወገን ላይ የሚያደር
ጉት ተፅዕኖና ጣልቃ ገብነትም
ሌላው ችግር ነበር አንዱን ብደ
ግፍ ሌላው ይነቅፈኛል (መናፍቅ
ይለኛል) በማለት በለዘብተኛነት
በማይገባ ፍርሀትና ይሉኝታ ጊዜ
አቸውን የአሳለፉ የቤተ ክርስቲ
ያን ተጠሪዎችም ጥቂቶች አልነበ
ሩም ።

ዛሬ ግን ይህ ሁሉ ችግር ተወግ
ዶአል በጠቃሚው ባህልና በእው
ነተኛው ሥርዓት ለመጠቀም የሚ
ያስቸግር ምንም ነገር የለም ጉዳዩ
እስከአሁን ድረስ አልታሰበበትም



አልተወሳም ነበረ ለማለት አይደ
ለም በእየአንድ አንዱ ሀሊና ሲን
ቀሳቀስ በእየአንድ አንዱ አንደ
በት ሲላወስ ኖርአል ከዚህም
አልፎ አጀንዳ ተይዞለት ጉባዔ
ተከፍቶለት በቤተ ክርስቲያኒቱ
ማዕከላዊ አስተዳደር በተደጋጋሚ
ታይቶና ተጠንቶ በዓለ ልደት
መሠረተ ዕለቱን መልቀቅ እንደሌ
ለበት ታምኖበት የተቀመጠ
ነው። አሁን ጥያቄው ለምን በተግ
ባር ላይ አይውልም? አልዋለም
ነው ።

ይህ ጽሑፍ በአሁኑ ወቅት ተዘ
ጋጅቶ የቀረበው የአለምክንያት
አይደለም አጋጣሚ ጊዜ ስለሆነ
ነው ዘመነ ዮሐንስ ዘንድሮ የባ
ተው በዕለተ ሐሙስ ነው እንዲ
ህም ከሆነ ገና (፳፰·፬) ማክሠኞ
ይሆናል ጥንተ ልደት (፳፱·፬)
ረቡዕ ይሆናል ዘመነ ዮሐንስ
ቅዳሜ ሲብት ደግሞ ገና (፳፰·፬)
ሐሙስ ስለሚሆን ጥንተ ልደት
(፳፱·፬) ዓርብ እንደሚሆን ማስታ
ወስ ይኖርብናል እንግዲህ በእነ
ዚህ አጋጣሚዎች ጊዜያት ነው
መለያየት የሚፈጠረው ፡ ይህም
አጋጣሚ ሁኔታ ምን ጊዜም በእየ
፳፱ኛው ዓመት እየተመላለሰ
ይመጣል በመሠረቱም ቢሆን ከአ
ራቱ ወንጌላውያን አንዱም ወንጌ
ላዊ የባተበትን ዕለት መልሶ ሊደ
ገም የሚችለው ይህን ቁጥር
ጠብቆ ነው ይህም ዓውደ ፀሐይ
ይባላል የቀመሩ ፍጻሜ ፳፰
ዓመት ነው መነሻው ፳፱ኛው
ዓመት ነው ።

ጥንተ ልደት ረቡዕ ሆኖ ከሆነ
በአሥራ አምስተኛው ዓመት
ዓርብ ይሆናል ዓርብ ሆኖ ከሆነ
ደግሞ ተመልሶ ረቡዕ ሊሆን የሚ
ችለው በአምስተኛው ዓመት
ነው።

ስለሆነም ቀን ልንሰጠው የማ
ይገባ ይሉንታም ሳያጠቃን እውነ
ቱን በግብር ላይ አውለን መጠ
ቀም ይኖርብናል ይህም ያስመስግ
ናል እንጂ አያስነቅፍም ።

# እግዚአብሔር ምስሌነ

ትርጓሜውም እግዚአብሔር
ከእኛ ጋር ነው ማለት ነው ።
ይህንንም የተነበየው ከክርስቶስ
ልደት በፊት በ፯ኛው መቶ ዓመተ
ዓለም የነበረው ነቢዩ ኢሳይያስ
ነው ። ትንቢቱም እንደሚከተ
ለው ይቀርባል ። እነሆ ድንግል
ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳ
ለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠ
ራዋለች ሲል ገልጾታል ። ትን
ቢተ ኢሳይያስ ም. ፯.፳፬ ።

ወንጌላዊው ማቴዎስም ይህን
ተከትሎ ስለ አማኑኤል ልደት
በጻፈው ወንጌል ወንድ ልጅም
ትወልዳለች እርሱ ሕዝቡን ከኃጢ
አታቸው ያድናቸዋል ስሙንም
ኢየሱስ ትለዋለች ሲል ለዮሴፍ
ካመለከተው በኋላ ሁኔታውን
በመቀጠል በነቢይ ከጌታ ዘንድ
እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ
ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማ
ኑኤል ትለዋለች የተባለው ይፈ
ጸም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆኖአል
ትርጓሜውም እግዚአብሔር
ከእኛ ጋር የሚል ነው ። የማቴዎስ
ወንጌል ም.፩ ፳፩ ፳፫

በዚህም አባባል ከላይ እንደተገ
ለጸው አማኑኤል ማለት እግዚአ
ብሔር ከእኛ ጋር ነው ማለት
ስለሆነ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ
አማኑኤል ከድንግል ማርያም
በሥጋ ስለተገለጸ ሁል ጊዜ ከእኛ
ጋር ይኖራል ማለት ነው እነዚህ

ከላይ የተጠቀሱት ለጌታችን የክ
ብር ስሞቹ በመሆናቸው በሕዝብ
ዘንድ የታወቁ ናቸው በተጨማ
ሪም አማኑኤል ማለት ቃል ሥጋ
ሆነ ማለት ነው ።

ወንጌላዊው ሉቃስም በም.፪-
፲-፲፬ እንደጻፈው ሕፃኑ አማኑ
ኤል በቤተ ልሔም በተወለደ ጊዜ
መንጋቸውን የሚጠብቁ እረኞ
ችና መላእክት አንድ ሆነው ክብር
ለእግዚአብሔር በ[illegible]የም ሰላ
ምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ
ይሁን እያሉ የልደቱን በዓል በደ
ስታ አክብረውታል ብሏል ።

እያንዳንዳችንም ይህን አርአያ
ተከትለን ፡ የልደቱን በዓል በየዓ
መቱ ማክበር ይገባናል አንዳንድ
ሊቃውንት በአራተኛው ዓመት
በዘመነ ዮሐንስ አማኑኤል ማክሰ
ኞና ሐሙስ ፳፰ ቀን የዋለ እንደ
ሆነ መግደፍ ይገባል በበነጋው
እሮብ ግን መጾም አለባቸው ሲሉ
ሌሎች ሊቃውንት ደግሞ ጥንተ
ልደቱ ስለሆነ የአማኑኤል ዕለት
ተጾሞ ረቡዕና አርብ መበላት
እንጂ መጾም የለባቸውም ሲሉ
አንዳንዶቹ ደግሞ ሁለቱም መበ
ላት እንጂ መጾም የለባቸውም
እያሉ የልደቱን በዓል ሕዝቡ በደ
ስታና በሰላም እንዳያከብረው ሲለ
ያዩትና ሲከፋፍሉት ኖረዋል ።
ይህን የመሰለው መለያየትም የተ
ፈጠረው በአፄ ሱስንዮስ ዘመነ
መንግሥት ከውጭ የመጡ የባዕ
ዳን ምሁራን እንከርዳድ የሆነውን
ትምህርታቸውን በስንዴው ላይ
ስለዘሩበት ነው በዚህ አኳኋን
መንግሥት ከሕዝብ ሕዝብም
ከመንግሥት ጋር ተለያየ ግማሹ



www.ethiopianorthodox.org

ታህሣሥ ፳፰ ቀን የአማኑኤል ዕለት ተገድፎ በማግሥቱ በ፳፱ መጾም አለበት ሲል ሌላው ደግሞ ሀያ ስምንትም ሀያ ዘጠኝም መበላት አለበት በማለት ተከፋፈለ በዚህ ምክንያት አያሌ ሊቃውንትና ካህናት ተገደሉ ተሰደዱ ምእመናንም እርስ በእርሳቸው ተከፋፈሉ ይህም ጭቅጭቅ ሳይበርድ እስከ ዘመናችን እንደደረሰ ሁላችንም የምናውቀው ነገር ነው እንዲህ ያለውም ጭቅጭቅ በእኛ አገር ብቻ ሳይሆን እህቶቻችን በሆኑት በኦሬንታል አብያተ ክርስቲያናትም ሊቃውንቱንና አማኞችን ለብዙ ጊዜ ሲያጨቃጭቅ ቆይቷል ይባላል በመጨረሻም ጭቅጭቅ አልበርድ ስላለ የግብፅ ሲኖዶስ በየአራት ዓመቱ ታኅሣሥ ፳፰ እና ታኅሣሥ ፳፱ እነዚህ ሁለቱ ቀኖች መጾም ሳይሆን ጥሉላት ሊበላባቸውና የደስታ ቀን ሆነው ሊውሉ ይገባቸዋል ሲሉ በመወሰኑ ጭቅጭቅ ሊበርድ ችሏል ።

በሀገራችን ግን ጭቅጭቅ ውስጥ ውስጡን ከመሄድ በቀር በተግባር ሳይገለፅ ቆይቶ ነበር በዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ግብፃዊው ጳጳስ አቡነ ማቴዎስ አንዳንድ ሊቃውንትንና ትምህርት ያነሳቸውን መሣፍንት ወደ ቤታቸው እየጠሩ ማግባባት ጀመሩ በመጨረሻም ለዳግማዊ ምኒልክ ይህ የልደት በዓል በየአራት ዓመቱ ከሚያጨቃጭቅ ታህሣሥ ፳፰ እና ታኅሣሥ ፳፱ ቀን የግብፅ ሲኖዶስ እንደወሰነው ቢበላ ይሻላል የሚል ሃሳብ አቀረቡ ዳግማዊ ምኒልክም ነገሩ እውነት ስለ መሰለችው የታወቁት ሊቃውንትና መሳፍንት አጥንተው እንዲያቀርቡ ወሰኑ ከአጥኚዎችም መካከል ፩ኛ ራስ መኮንን ፪ኛ ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ፫ኛ ራስ ዳርጌ ሲሆኑ ከሊቃውንቱ መካከል ደግሞ ፩ኛ እጨጌ ገ/ሥላሴ ፪ኛ አለቃ ገብረሃና ፫ኛ መምህር አካለ ወልድ ነበሩ እቴጌ ጣይቱም ሰውን የማግባባትና ተናግሮ የማሳመን እድል ስለነበራቸው ሕዝብንና መንግሥትን የሚለያይ ሊቃውንትንም ሲያጨቃጭቅ የሚኖር እንዲህ ያለ መጥፎ ነገር ይጠና ማለትዎ በመጀመሪያ ጊዜ ፍቅርንና ታማኝነትን ከሕዝቡ ዘንድ የሚያሳጣዎ ነው ብለው ስለነገሩዋቸው ጥናቱ እንዲቀር ተደረገ ቀጥለውም እቴጌ ጣይቱ አቡነ ማቴዎስን አስጠርተው እርስዎን ያመጣንዎት ክህነት እንዲሰጡ እንጂ ሀገራችንንና ቤተ ክርስቲያናችንን እንዲከፋፍሉ አይደለም ። በግብፅ ተወስኗል ስለሚሉት ግብፅ ሲሄዱ እዚያው ይፈጽሙት ሲሉ ገሠጿቸው ጳጳሱም ስለደነገጡ ነገሩን እርግፍ አድርገው ተውት ነገሩም እንደ በረዶ ቀዝቅዞ ቀረ ።

ነገሩ በዚህ ላይ እንዳለ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊነት ቢኖራትም ለ፩ሺ፮፻ ዓመታት ያህል የራሷ የሆነ ሲኖዶስ ሳታቋቁም ቆይታለች በእነዚህ ዓመታት ውስጥ ለሁለት ጊዜ የሲኖዶስ ውሳኔ ተወሰነ ተብሎ ቢነገርም ከእስክንድርያ ተወስኖ የተላከ እንጂ ኢትዮጵያ በሚገኘው መንበረ ጵጵስና አልነበረም ከሁለቱ መካከል አንደኛው ውሳኔ ሕዝብንና ቤተ ክርስቲያንን የሚያለያይ በቤተ ክርስቲያን መካከል ሰላምንና ፍቅርን የሚያሳጣ ውሳኔ ነበር ይኸውም ከላይ እንደተጠቀሰው ታህሣሥ ፳፰ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓ.ም በዘመነ ዮሐንስ አማኑኤል ሐሙስ ቀን ውሎ ነበር በማግሥቱ አርብ ቀን ጥንተ ልደቱ የነበረው ባለ እግዚአብሔር አርብ ቀን ውሎ ስለነበር ሐሙስም ዓርብም ይበላ ሲል የግብፅ ሲኖዶስ አዟል በማለት ግብፃዊው ሊቀ ጳጳስ የነበሩት አቡነ ቄርሎስ አዘዙ ደብዳቤም ወደየገዳማቱና ወደየአድባራቱ እንዲተላለፍ አደረጉ ይህንንም የኃይለሥላሴ መንግሥት ስለደገፈው እና በየግዛቱ ያሉትን ገዢዎች ግብር እንዲያበሉ በደብዳቤም በስልክም አስተላለፈ ሕዝቡና ካህናቱ ግን አንድ ወገን ሆነው ዓርብ ይጾማል እንጂ አይበላም ሲሉ ታላቅ ተቃውሞ አነሡ ። አንዳንድ ያወገዙ የገዳማትና የአድባራት አስተዳዳሪዎች ታሰሩ ከእነዚህም መካከል ከእልቅናቸው የተሻሩ ነበሩ ዓርብን ሲጾሙና ሲያጾሙ የዋሉት ምሁራን በመሾምና በመሸለም ፈንታ ፀጋና ቅባት ናቸው የሚል መጥፎ ስም ተሰጣቸው ሲበሉና ሲያስበሉ የዋሉት ግን እውነተኛ የኦርቶዶክስ አማኞች ናቸው የሚል ስም ተሰጥቷቸው ነበር በዚህም መጥፎ ድርጊት ምክንያት በቤተ ክርስቲያን ሰላምና ፍቅር ሰፍቶ ጥልና ጭቅጭቅ ሰፍኖ ታላቅ መሰቃየት ተፈጥሮ ነበር ።

በጣም የሚያስደንቀው ደግሞ በካህናትና በሕዝብ ዘንድ ተወዳጅነት የነበራቸው የመካነ ኢየሱስ መነኩሴ አባ ዘገየ አማኑኤል የእመቤታችን በዓል እንጂ እራሱን የቻለ በዓል አይደለም በመሆኑም በየአራት ዓመቱ ታኅሣሥ ፳፰ ቀን እና በሌሎችም ዓመታት ገሀድ ሆኖ ከመጾም በቀር የመግደፊያ በዓል ሊሆን አይገባውም ለዚህም መረጃ የሚሆነን በጎንደር ሀ/ስብከት በእስቴ ወረዳ በቁት አቡነ አረጋዊና በመሀልጌ ዕዮን በሌሎችም አብያተ ክርስቲያናት ከግራኝ በፊት የተጻፉት ስንክሳሮች ለእመ ኮነ አይሉም ያሬድም በድጓው ለሌሎቹ ለእመ ኮነ ሲጽፍ ለአማኑኤል ግን ለእመ ኮነ አልጻፈም ሐዋርያትም በዲዲስቅልያ ፲፰፻፲፰ ሊቃውንትም በፍትሐ ነገሥት በጥንተ ልደቱ ታህሣሥ ፳፱ ቀን ይገደፍ አሉ እንጂ ታህሣሥ ፳፰ ቀን የአማኑኤል ዕለት ይገደፍ የሚል ጽሑፍ አልጻፉም ። አላስተማሩም ይህንንም በማድረጋቸው ሌላው ቀርቶ ይወዳቸው የነበረው የመካነ ኢየሱስ ሕዝብ እንኳ ፍቅሩን ቀነሰባቸው የበተኑትም ጽሑፍ ዛሬም በእያንዳንዱ ሰው እጅ ይገኛል ይህም ጭቅጭቅ ሳይበርድ እስከ ማይጨው ጦርነት ድረስ ቆየ ሕዝቡም በዚህ አቋሙ ስለነበር በጦርነቱ ጊዜ ጥቂቱ ሲዋጋ አብዛኛው ግን ወደኋላ አፈገፈገ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴም ድል ሆነው ወደ አዲስ አበባ ሲመለሱ በየመንገዱ ታላቅ ጦርነት ገጠማቸው ይኸውም የኢትዮጵያ ሕዝብ እምነቱንና ባህሉን የሚነካበትን ስለማይወድ በንጉሡ ቂም በመያዙ ነው ። ይህ ሁሉ ተቃውሞ የደረሰባቸው በዚህ ምክንያት እንደሆነ አንዳንድ ሰዎች ይናገራሉ ።

እንደገና ደግሞ በ፲፱፻፵፪ ዓ.ም በዓለ እግዚአብሔር አርብ ቀን ስለዋለ አብዛኛው ይጾም ሲል ጥቂቱ ደግሞ መበላት አለበት የሚል ጭቅጭቅ ተነሥቶ እንደነበር ይታወሳል ይህንኑ ጭቅጭቅ ለማብረድ ሲባል በ፲፱፻፵፯ ዓ.ም በዘመነ ዮሐንስ አማኑኤል ታህሣሥ ፳፰ ቀን ማክሰኞ ቀን ስለዋለ ማክሰኞ እንዲበላና ረቡዕ ታህሣሥ ፳፱ እንዲጾም በመጀመሪያው ፓትርያርክ በአቡነ ባስልዮስ ሰብሳቢነት የጳጳሳት ስብሰባ ተደርጐ ነበር ። የተወሰነውም ውሳኔ ለየአብያተ ክርስቲያናቱ ተላልፎ ነበር። ይሁን እንጂ በዚያን ጊዜ የነበረው መንግሥት የቤተ ክርስቲያኗ አስተዳደርና የሃይማኖት ጠባቂ እኔ ስሆን እኔን ሳያስፈቅድ ሲኖዶስ ለምን ወሰነ በማለት ውሳኔውን ተቃወመ ቀጥሎም ሶስት ሰዎችን ልኮ በየቤተ ክርስቲያኑ እየተዘዋወሩ ሌሊት ደወል እንዲያስደውሉ ጧት ተቀድሶ እንዲበላና የሲኖዶስ ውሳኔ እንዲሻር አደረገ ያንጊዜ በአዲስ አበባ ከነበሩት ፴፪ አብያተ ክርስቲያናት መካከል አራቱ አድባራት ፩ኛ ታዕካ ነገሥት በአታ ፪ኛ መንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ፫ኛ መንበረ ፀሐይ እንጦጦ ማርያም ፬ኛ ደብረአሚን ተክለሃይማኖት የሲኖዶስን ውሳኔ አክብረውና ጾም ውለው ሲቀድሱ የቀሩት ግን ጧት ቀድሰዋል በዚህም በሕዝብና በካህናት መካከል ጭቅጭቅ ተነስቶ በቤተ ክርስቲያንም ሰላምና ፍቅር ጠፍቶ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው መንግሥትም ይህን መጥፎ ድርጊት የተቃወሙትን የአራቱንም አድባራት አለቆች አስጠርቶ ውሎ እንዲበላ በማድረጋቸው ከባድ ወቀሳ ወቅሷቸው እንደነበር ከታሪክ ለመረዳት ይቻላል በአሁንም ሲኖዶስ ይኸው ውሳኔ እንዲከበር ትእዛዝ ተላልፏል ይህን ሁሉ ለመዘርዘር የፈለግነው ጠንካራ የነበሩት የሃይማኖት አባቶቻችን እየታሰሩና እየተወቀሱ ያቆዩትን እምነትና ባህል እኛም አክብረን እንደናስከብረው ሕዝቡንም ይልተማሩ ሰዎች እንዳይከፋፈሉት ዘንድሮ የሚከበረውም ታህሣሥ ፳፰ ፲፱፻፹፬ ዓ.ም የአማኑኤል ዕለት እንደሚገደፍና ታህሣሥ ፳፱ ቀን ደግሞ የሚጾም መሆኑን ቀደም ብለን ማስተማር ይገባናል ።

የዚህም ሓላፊነት ያለበት ቅዱስ ሲኖዶስ ስለሆነ ትምህርት ያነሳቸው አንዳንድ የንስሐ አባቶች ቀሳውስት ታህሣሥ ፳፱ ቀን ይበላል አይጾምም እያሉ ሕዝቡን እንዳያሳስቱ ለማድረግ የየአድባራቱና የየገዳማቱ አስተዳዳሪዎችና መምህራን ለሚሰበሰበው ሕዝብ ትምህርት እንዲሰጡ እየዞሩም እንዲያስተምሩ ቢደረግ መከፋፈልና መለያየት ቀርቶ አማኞች አንድ ስለሚሆኑ ቤተ ክርስቲያንም ሆነች ሕዝቡ ሰላም ያገኛሉ ። ስለዚህ ትምህርት የማያሻሽለው ነገር ስለሌለ ሁላችንም ለማስተማር እንሥማራ እግዚአብሔርም ከእኛ ጋር እንዲሆንልን ሕጉን በመጠበቅ ትእዛዙን በመፈጸም እንኑር ።

አለቃ ነቢየልዑል ዮሐንስ

---

## ጤናችን…

(ከገጽ ፳፬ የዞረ)

መጀመር እስከ መጨረሻ መከተብ ።

፪) የተነከሱት አብደል ተብሎ የተጠረጠረ እንስሳ ከሆነ ቶሎ ብሎ ቁስሉን በውሃና በሳሙና ማጠብ ቁስሉን አለመስፋት እንስሳው ካልተገኘ ክትባት መውሰድ ይገባል ።

አቅራቢ
መላከ ሕይወት
ይትባረክ ዓለሙ



www.ethiopianorthodox.org

# ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ በሰሜን ወሎ ሀገረ ስብከት ውስጥ ያደረጉት ሐዋርያዊ ጉዞ

ብፁዕ አባታችን አቡነ ቄርሎስ በሰሜን ወሎ ሀገረ ስብከት ውስጥ ለ፪ ዓመታት ያህል በደረሰው ችግር ምክንያት ተቋርጦ የነበረውን የሰበካ ጉባኤ አቋም ለማጠናከርና ለማቋቋም ሀገረ ስብከቱ ባወጣው ፕሮግራም መሠረት ከየጁ አውራጃ ቤተ ክህነት በመነሣት በራያና ቆቦ ፡ በወፍላ አውራጃ ቤተ ክህነት በመዘዋወር ለ፲፫ ቀናት ያህል በየአውራጃዎቹ ውስጥ የሚገኙትን የሰበካ ጉባኤ አባላትንና የቤተ ክህነት ሠራተኞችን እንዲሁም ካህናቱንና ምዕመናኑን ለማጽናናትና ብሎም ለማጠናከር በአደረጉት ሐዋርያዊ ጉዞ የተገኘው ውጤት በጣም የሚያስደስት ሆኖ በመገኘቱ ለወደፊቱም የሥራ እንቅስቃሴ የሚረዳ ሆኖ ተገኝቷል ።

ምክንያቱም ምዕመናኑ ሃይማኖቱን ጠባቂ የሃይማኖት መሪውን አክባሪ በመሆኑ ብፁዕነታቸው በመካከሉ ስለተገኙ የተሰማውን መንፈሳዊ ደስታ በከፍተኛ አቀባበል ገልጿል ይኸውም ይታወቅ ዘንድ ሕዝቡ ከብፁዕነታቸው ፊት ቀርቦ መስቀል ለመባረክ ያለው ጉጉት በጣም ያስገርም ነበር በተጨማሪም አዝመራውንና አትክልቱን በእጁ ይዞ በማስባረክ ተራ እስከሚደርሰው ድረስ ያለው ጉጉት በጣም ያስደንቅ ነበር የዚያን ጊዜ ካሜራ የለንም እንጂ ቢኖረን ኖሮ እያባዛን በየአህጉረ ስብከቶቹ በአስራጨን ነበር ግን እኛ በሰሜኑ ክፍል የምንገኝ በመሆናችን ንብረታችንና ገንዘባችን በጦርነቱ ምክንያት የደቀቀ ስለሆነ ከማዘን በስተቀር ምንም ለማድረግ ባለመቻላችን በጣም እያዘን ነው ።

ሆኖም ግን ያዘነ የተከዘ ኀዘኑና ትካዜው በደስታ እንደሚለወጥ ስለምናምን የአለፈውን ኀዘን ተቀብሎ አሁን ሰላም የሰጠን አምላክ ወደፊት ያለው ዘመን የሰላምና የደስታ የብልጽግናና የሥራ ጊዜ ሆኖልን በአለን ኃይል ሰርተን ነፃነታችንን አግኝተን ሃይማኖታችንን ጠብቀን እንደምንኖር እንጠራጠርም የብፁዕነታቸውም ጸሎትና ቡራኬ ስለማይለየን በየሥራችን ተመድበን በጦርነቱ የደቀቀውን ኢኮኖሚያችንን እንደምንገነባ እናምናለን ።

በፁዕ አባታችንም በሰሜኑ ክፍል የደረሰውን ችግር ለማየትና ምዕመናኑን ለማጽናት ከግሸን ደብረ ከርቤ ወደ ደሴ እንደተመለሱ ደከመኝ ልረፍ ሳይሉ ጉዞአቸውን ወደ ሰሜን ወሎ ሀገረ ስብከት በመቀጠል በ፳፱ ፩ ፹፱ ዓ.ም ወልድያ ከተማ ከሚገኘው መንበረ ጵጵስናቸው ደርሰው አዳር ከአደረጉ በኋላ በ፳፫ ፩ ፹፱ ዓ.ም እሁድ መንበረ ንግሥት ኪዳነ ምሀረት ቤተ ክርስቲያን ተገኝተው ተናፋቂ ለሆኑት ምዕመናን ሰፋ ያለ ትምህርት ከሰጡ በኋላ ምዕመናኑም ብፁዕነታቸው በቦታው በመገኘታቸው የተሰማቸውን ደስታ ገልጸውላቸዋል ብፁዕነታቸውም የተሰበሰበውን ምዕመናን እያንዳንዱ በመባረክ ስለ አሰናበቷቸው በኋላም ወደየ ቤታቸው ተመልሰዋል በዚሁ ዕለትም የሰንበት ተማሪዎችን ከት ቤታቸው ድረስ በመሄድ ትምህርት ሰጥተው ተማሪዎችን አጽናንተው አስማምተው ከጨረሱ በኋላ ወደ ገነት ሀ/ማ በመሄድ ከምሽቱ ፩ ሰዓት ድረስ ት/ሲሰጡ ቆይተው ወደ መንበረ ጵጵስናቸው ተመልሰዋል ።

በ፳፯/፩/፹፱ ዓ.ም

በሀገረ ስብከቱ ሰብሳቢነት በየጁ አውራጃ መሰብሰቢያ አዳራሽ የተጠሩትን የጉባኤ ላፍትንና የህብሩን የሰበካ ጉባኤ አባላትንና ካህናቱን እንዲሁም በወልድያ ከተማ የሚገኙትን ጭምር በማሰባሰብ በአለፈው ዘመን ስለአጋጠማቸው ችግርና ስለ ሰበካ ጉባኤ መጠናከር ስለ አስተዋጽኦ አከፋፈል ስለ ቤተ ክህነት ሠራተኞችና ስለ ሰበካ ጉባኤ አባላት የሥራ ግንኙነት ወዘተ በመሳሰሉት አጀንዳዎች ላይ ለመወያየት በተደረገው ጥሪ መሠረት ከ፪፻ በላይ የሚሆኑ ካህናትና የሰበካ ጉባኤ አባላት በተገኙበት ብፁዕነታቸው በስብሰባው ላይ ተገኝተው ሰፋ ያለ ትምህርትና መመሪያ ሲሰጡ ውለዋል በመጀመሪያ ግን ስለ ስብሰባው ዋና ዓላማ የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ መልአከ ገነት ተስፋ ወ አብርሃም አጠር ያለ የመግቢያ ንግግር አድርገዋል በመግቢያ ንግግራቸውም የዚህ ጉባኤ ውይይት ዋና ዓላማ ተራርቆ የነበረውን የሰበካ ጉባኤ አሠራር ለማቀራረብ ከአባላቱ መካከልና በቤተ ክህነት ሠራተኞች መለያየት ሳይኖር ሁሉም በአንድ ልብ ሆኖ መስራት ያለበት መሆኑን እንዲሁም ቀደም ሲል በነበረው ችግር ምክንያት የመንበረ ጵጵስናው ሀኖ የሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት ንብረት አንድም ነገር ሳይባክን በአካባቢው በሚገኙት ካህናትና ምዕመናን ተጠብቆ መቆየቱ እጅግ የሚያስመሰግንና የሚያሀናቱ ማህበራዊ ኑሮ እንዲሻሻል ከምዕመናን የሚገኘው ማንኛውም ገቢ በተገቢው መንገድ በሕጋዊ ካርኒ እየተሰበሰበ ወጭው በትክክል እንዲወጣ በመካከላችን መለያየት ሳይኖር እንደ መጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች አንድ በሊቀ ካህናት ተስፋ ሲሳይ ላይ ስለሆነ የሊቀ ካህናቱ ጉዳይ በአስተዳደሩ በኩል ታይቶ መመሪያ የሚሰጥበት መሆኑን ገልጸው ስብሰባው በጸሎት ተዘግቶ የጉባኤው ተሳታፊዎች ቡራኬ እየተቀበሉ ወደየቤታቸው ተመልሰዋል ።



ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ በሰሜን ወሎ ሐዋርያዊ ጉዞ ሲያደርጉ

ኮራ መንፈሳዊ ተግባር ሆኖ ስለተገኘ ይህን ለፈጸሙ ካህናትና ምዕመናን ከፍተኛ ምስጋና አቅርበዋል ።

ከዚህ በመቀጠል ብፁዕነታቸው ከቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ከግብረ ሐዋርያት ምዕ. ፫ እና ፮ የሚገኘውን ቃል በመጥቀስ አንድነታችን እንዲጠነክር ክርስትናችን ተጠብቆ እንዲኖር የቤተ ክርስቲያን ቅርስ እንዲጠበቅ ልጆች መንፈሳዊ ትምህርት እየተማሩ እንዲያድጉ ሰበካ ጉባኤ ተቋቁሞና ተጠናክሮ አብያተ ክርስቲያናቱ እንዲቀደሱና እንዲወደሱ የካልብ ሆነን ባለን መንፈሳዊ ተግባር ጸንተን መኖር ይገባል በማለት በጉባኤው ሰፋ ያለአባታዊ ትምህርትና መመሪያ ሰጥተዋል በዕለቱ በከፍተኛ ደረጃ ውይይት ሲደረግበት የዋለው በቤተ ክህነት ሠራተኞችና በሰበካ ጉባኤ አባላት እንዲሁም በካህናቱ መካከል ያለውን አለመግባባት ሰፋ ባለ ሁኔታ ከሰሙና ከአዳመጡ በኋላ ሁኔታው በሰላም እንዲፈታ አድርገው ወደፊት ሁሉም በየአሉበት በሰላም ሥራቸውን እየተግባቡ እንዲሠሩ መመሪያ ሰጥተዋል በዕለቱ የተነሳው ጭቅጭቅ

በ፳፯/፩/፹፱ ዓ.ም ለ፳፰/፩/፹፱ ከሌሊቱ በ፲፩ ሰዓት ተነስተው ጉዞአቸውን ወደ ቆቦ ከተማ ከሠራተኞቻቸው ጋር በመሆን ቀጥለው ደ.ጋጉ ደ/ሰላም መድኃኒዓለም ሲደርሱ ካህናቱና ምዕመናኑ ከፍተኛ ድምቀት በአለው ነኳኳን ከተቀበሏቸው በኋላ ቅዳሴ አስቀድሰው እንደወጡ ለተሰበሰበው ሕዝበ ቤተክርስቲያን እምብዝኃ መከራ ሀማሞሙ ፈድፈደ ፍስሐሆሙ ብለው በመነሳት በጣም ደስ የሚያሰኝ ትምህርት ከሰጡ በኋላ በአንድ አንድ ምክንያት ተጣልተው ወደ ግድያ የደረ





www.ethiopianorthodox.org

ሱና በጠቅላላ ምዕመናኑን በዚሁ ጉዳይ ሲጨነቅበትና ሲጠበቡበት የነበረውን ጸብና ክርክር አብር ደው የሰላም ኮሚወቴ በማቋቋም ለወደፊቱም በአካባቢው ጠብና ክርክር እንዳይነሳ በማድረግ ተጣ ልተው የነበሩትን ወንድማማቾች ብፁዕነታቸው በመካከላቸው ተገ ኝተው አስማምተው ከአበቁ በኋላ የተቋቋሙት ኮሚቴዎች በዚሁ መልክ የሚጣሉትን ሁሉ ጊዜ ሳይወስዱ እንዲያስማሙ እና እንዲያስታርቁ በማለት መመሪያ ሰጥተው የተጣሉትን አስታር ቀው ጸሎት አድርገው በሰላም ወደ የቤታቸው እንዲሄዱ ከአደ ረጉ በኋላ በአካባቢው የሚገኙት ምዕመናን ብፁዕነታቸው ባደረ ጉት የማስታረቅ ተግባር የተሰማ ቸውን ደስታ ከልብ አድንቀዋል ከዚህ በኋላ መዘምራኑ በየተራ እየቀረቡ ስለተሰማቸው ደስታ የመውደስ ቅኔ አበርክተዋል ።

በዚሁም ዕለት ብፁዕነታቸው የሰንበት ተማሪዎችን ሲያስተም ሩና ሲያጽናኑ ቆይተው ለማረፊያ ወደ ተዘጋጀላቸው ቦታ ሄደው አዳር ሆኗል ።

በ፳፰/፩/፹፬ ዓ.ም ከሌሊቱ ፲፩ ሰዓት ሲሆን በደብረ ዐሐይ ቆቦ ማርያም ቤተ ክርስቲያን በመገ ኘት በርከት ላሉ ዲያቆናትና ቀሳ ውስት የሥልጣን ክህነት ማዕረግ ሰጥተው ከአበቁ በኋላ በቆቦ ከተማ ውስጥ የሚገኙትን የ፲፱ቱን አድባራት አስተዳዳሪዎችና የሰ በካ ጉባኤ አባላትን ካህናትንና የቤተ ክህነት ሠራተኞችን እንዲ ሁም የሀገር ሽማግሌዎችን አሰባስ በው ሲያነጋግሩ ቆይተው መመሪ ያና ምክር ሰጥተው ሁሉም በየ ሥራ ድርሻው በስምምነት የቃለ ዓዋዲውን ሕግ ጠብቀው እንዲ ሠሩ በማስረዳት ቃለ ቡራኬ ከሰጡ በኋላ በተጨማሪ መዘም ራኑ ቅኔ በርክተዋል ።


ይቀጥላል ።

# በጠ/ቤተ ክህነት አዲስ አስተዳዳሪ ተሾሙ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋ ሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ጠ/ጽ/ቤት አዲስ ሥራ አስኪያጅ ተሹሟል ፤ ሥራ አስኪያጁ ከጠ/ሚኒስቴር ቤተ ክህነትን እንዲያስተዳድሩ የተሾ ሙት ከመስከረም ፳፰ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ/ም ጀምሮ ነው ።

አዲሱ ሹም አቶ ዘመነ ህላዊ ይባላሉ ፤ ጥቅምት ፮ ቀን ፹፬ ዓ/ም በስብከተ ወንጌል አዳራሽ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና በመንበረ ፓትርያርክ ጠ/ጽ/ቤት የሚሠሩ ሠራተኞች በሙሉ ተሰብስበው ከሥራ አስኪያጁ ጋር ትውውቅ አድርገዋል ፤ በትውውቁም ጊዜ በመጀመሪያ ብፁዕ አቡነ ዜና ማር ቆስ የቅዱስ ሲኖዶስ ጊዜያዊ አስ ተዳደር ሰብሳቢ ጉባኤውን በጸ ሎት ከፍተዋል ።

ቀጥሎም አዲሱ ሥራ አስኪ ያጅ አቶ ዘመነ ህላዌ ራሳቸውን ለሠራተኛው አስተዋውቀው አጠር ያለ ገለጻ አድርገዋል ፤ ባደረጉትም ገለጻ ከ፲፪ ዓመታ ቸው ጀምረው በመንበረ ፓትርያ ርክ ግቢ የቤተ ክርስቲያናችን ትምህርት እየተማሩ ማደጋቸው ንና ከዚያም ወጣ ብለው በሰላሌ አውራጃ ሥሬ መድኃኔ ዓለም ከአ ለቃ ጥበቡ ገሜ ቅኔ ዕማራቸውን ተናግረዋል ፤ በመቀጠልም ወደ በጌምድር ጠ/ግዛት ሄደው ደብረ ታቦር አውራጃ እስቴ ወረዳ መካነ ኢየሱስ ከነበሩት መምህር ገብረ ጊዮርጊስ የመጽሐፍ ትርጓሜን እንደተማሩና ከዚያም እንደገና ወደ አዲስ አበባ ከተማ ተመል ሰው በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ገብተው ዘመናዊ ትምህር ታቸውን ተምረው ከፈጸሙ በኋላ ወደ አሜሪካ ሄደው መጀመሪያ የባችለር ድግሪ ፤ ቀጥሎም በክር ሚኖሎጂ ጥናት የማስትሬት ድግሪ ተቀብለው ወደ እናት ሀገራ ቸው መመለሳቸውን ገልጸው ወደ ሀገራቸው ከተመለሱም በኋላ በተ



አዲሱ ሥራ አስኪያጅ
አቶ ዘመነ ሕላዌ እኒህ ናቸው

ለያዩ የሥራ ክፍሎች እየተመደቡ ሀገራቸውን ማገልገላቸውን ተናግ ረዋል ።

አቶ ዘመነ ህላዊ ንግግራቸውን በመቀጠል በዚህ የተሰበሰባችሁ አባቶችና ወንድሞቼ እኔ የእናንተ አገልጋይ ታዛዥ ተላላኪ ነኝ እንጂ አዛዣችሁ እንዳይደለሁ እንድታውቁልኝ እፈልጋለሁ ፤ ከሁላችሁ ትብብርን አንድነትን ፍቅርን ሰላምን እፈልጋለሁ ፤ ከብ ፁዓን አባቶችም በተገቢው መን ገድ መልካም ምክርን እፈልጋ ለሁ፤ የምሠራው እንደ ኢትዮጵያ

# የደብረ ኃይል ራጉኤል የሰንበት ት/ተማሪዎች ፳፫ኛውን ዓመት በዓላቸውን አከበሩ

አዲስ አበባ ከተማ የሚገኘው የደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ት/ቤት ተማሮች የተመሠረተበትን ፳፭ ዓመት ያከበሩት ጥቅምት ፱ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ/ም ነው ።

በዚሁ ዕለት ከ፮ ሰዓት ጀምሮ ጥሪ የተደረገላቸው አባቶችና እና ቶች ወጣቶችና ታዳጊ ሕፃናት የተመደበላቸውን ቦታ መያዝ ጀምረዋል ። ፤ በ፯ ሰዓት ተኩል ብፁዕ አቡነ በርናባስ የአዲስ አበባ ሀ/ስብከት ሊቀ ጳጳስና የኢ ትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ አባል መምህር ገብረ ማርያም አጽብሐን አስከትለው ከስፍራው ሲደርሱ የሰንበት ትምህርት ቤት ኃላፊ ወጣት ገዛህኝ በተማሮቹና በራሱ ስም እንኳን ደኅና መጡ በማለት ተቀብሏቸዋል ሁለት ሕፃናትም እቅፍ አበባ አበርክተውላቸዋል ።

ሰባት ሰዓት ተኩል ሲሆን ብፁዕ አቡነ በርናባስ የአዲስ አበባ ሀ/ስብከት ሊቀ ጳጳስ በዓ ሉን በጸሎት ከከፈቱ በኋላ የማኅ



በየወቅቱ የሰንበት ት/ቤቱን የመሩት ወጣቶች ከደብሩ አስተዳዳሪ ጋር

በሩ ሊቀ መንበር ተማሪ ገዛህኝ ስለ ማኅበሩ አመሠራረትና ከየት ተነሥቶ ወደየት እንደደረሰ ሰፋ ያለ ንግግር አድርጓል ። ቀጥሎም በተማሮቹ የተዘጋጀ ልብን የሚ መስጥ ያሬዳዊ ዜማ ተሰምቶ ሲያ በቃ ልዩ ልዩ ግጥሞች ተነበዋል ።

ከዚያም በመቀጠል ከ፳፫ ዓመት ጀምሮ በየጊዜው በፈረቃ በሊቀ መንበርነት ማኅበሩን የመ ሩና አሁንም በሥራ ላይ የሚገኙ ወጣቶች ልዩ ልዩ ጥያቄዎች ቀርበ ውላቸው ገንቢና አርኪ የሆኑ መልሶችን ሰጥተዋል ፤ ከጥያቄ ውና ከመልሱ ቀጥሎ ትምህርት አዘል ድራማ ቀርቦ ታይቷል ።

ድርማው አክዓብና ኤልዛቤል ናቡቴ የተባለውን ሰው ርስት ለመንጠቅ ሲሉ እርሱን እንዳስገ ደሉትና በመጨረሻም የሠሩት ግፍ በራሳቸው ላይ እንደሚደርስ እግዚአብሔር በነቢዩ በሚልክ ያስ አድሮ አንደ ዘለፋቸውና የሚ ደርስባቸውንም መከራ እንደነገራ ቸው ያስረዳል ሚልክያስ ነቢዩ በተናገረው መሠረት አክዓብ ከጠ ላቶቹ ጋር ጦርነት ግጥሞ ሲዋጋ በጦር ተወግቶ ሲሞት ኤልዛቤ ልም በመስኮት ተወርውራ ወድቃ ሕይወተ ሥጋዋ ስላለፈ ደሟንም ውሾች እንደላሱት የሚገልጽ ነበር ።

የድራማው አቀራረቡና ይዞ ታው በአማረና በረቀቀ ጥበብ ስለነበር የተመልካችን ሐሣብ ጉትቶ ወስዶ በዓይኑ ልቡና ከአክ ዓብና ከኤልዛቤለ እንዲሁም ከና ቡቴ ጋር የሚያነጋግር ነበር ዝግ ጅቱ ተመልካችን የሚያስደስት ከመሆኑ የተነሣ ከ፯—፲፩·፴ ተቀ ምጦ የተመለከተው ሕዝብ አንድ

ዊነቱ በትክክል ነው ፤ ተንኮለኛ ያልሆነ ነገር ሊለጥፍ ይችላል ግን ሕግን በመከተል የምሠራ ስለሆነ በሥራዬ ድክመት አላሳይም ከሁ ላችሁም ጋር ተባብረን ለቤተ ክር ስቲያናችን እንሠራለን ፤ እንደዚ ሁም ስላልኩኝ ከሌብነትና ከቅጥ ፈት ጋር ተባብሮ ለሚመጣ ሰው ትዕግሥት አይኖረኝም ካሉ በኋላ ከዛሬ ጀምሮ ለሁላችንም መሥ ሪያ ቤቱ ክፍት ነው ለምንሠራው ሥራ ሁሉ እግዚአብሔር ማስተዋ ሉን ይስጠን በማለት ንግግራቸ ውን አጠቃለዋል ። ከዚያም በኋላ ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ በጸሎት ቡራኬ አሳርገው የትውውቁ ሥነ ሥርዓት ተፈጽሟል ።
የዜና አቅራቢ ቁ.ሊ.ኀ.ኤሣነ ወርቅ በዛብኅ



www.ethiopianorthodox.org

# የሴቶች ዓምድ

## መንፈሳዊ አገልግሎት

አዘጋጅ መዓዛ አስማማው

አገልግሎታቸውንና ስጦታቸውን በትህትናና በልግስና የሚያደርጉ ምእመናን ጥቂቶች አይደሉም ። መቸም በዓለም ላይ በሀብታቸው ብዛት ተወዳዳሪ የሌላቸውን ሰዎች ስንመለከት ግን አንድ የሚጎድላቸው ነገር ይኖራል ። በአንጻሩ ደግሞ ሁሉም ተሟልቶ ከልዑል እግዚአብሔር የተሰጣቸው እንዳሉም አይካድም ።

በአሜሪካ ታዋቂና ዝነኛ በሀብቱም ገናና የነበረው ሮክፌለር ቁጡና ንፉግ እንደነበር ታሪኩ ይናገራል ። ከሠራተኞች ጋር ብቻ ሣይሆን በሕዝቡም ዘንድ ተወዳጅነትና ተግባቢነት አጥቶ ይኖር ነበረ ። ነገሩ ለራሱም ደንቀው አንድ ቀን የሚከተለውን ተናገረ። "ተወዳጅነትም ሆነ ተግባቢነት እንደ ስኳርና ቡና በየሱቁ የሚሸጡ ቢሆን ኖሮ ሀብታም እንደ መሆኔ መጠን ለመግዛት ማንም ባልቀደመኝም ነበር ። ከልዩ ልዩ ሀገርም በሸቀጥ መልክ ሆነው



ወ/ሮ ማርያ ሊዮኒ
እኒህ ናቸው

በንግድ ልውውጥ የሚገዙ ቢሆን ባለኝ ሀብት ገዝቼ በተጠቀምኩበት ነበር ። ነገርግን ተወዳጅነትና ተግባቢነት በሀብት ብዛት ስለማ ይገኙ በገንዘብም ሊገዙ ስለማይችሉ ትርፍ ድካም ብቻ ነው ። የሆነ ሆኖ ተወዳጅነትና ተግባቢነት የሚገኙት ተመሳስሎ በመኖር በትእግሥት አብሮ በመብላትና በመጠጣት ለሌላው አገልግሎትን በመስጠት በመተዛዘን በመሀኑ ደሃና ሀብታም የማይለያዩበት የማያልቅ በረከት ነው ።" ብሏል ።

በዚህች ባለንባት ምድር ሥፍር ቁጥር የሌላቸው ሀብታሞች አሉ። ሊባል የሚቻለው በሀብታቸው መጠቀም ሲችሉ ብቻ ነው ። አጠቃቀሙን የማያውቁበትና የመግባባት ችሎታ የሌላቸው ግን ሥራቸውም ሀብታቸውም ፍሬ ቢስ ሆኖ ይቀራል ።

አንዳንድ የአፍ ሣይሆን የሥራ ክርስቲያኖች በማኅበራዊ ኑሮ በኩል ወገንን ለመርዳት ችግረኞችን ከችግራቸው ለማላቀቅ ፣ ጧሪ ቀባሪ የሌላቸውን ሽማግሌዎች ለመደገፍ ፣ አሳዳጊ ያጡ ሕፃናትን ለማሳደግ ፣ የፈረሱ አብያተክርስቲያናትን ለማሳደስ የሚያደርጉትን መልካም ሥራና የሚሰጡትን መንፈሳዊ አገልግሎት ።

፩ኛ/ ወደፊት እንዲገፉበት የሞራል ድጋፍ ለመስጠት

፪ኛ/ ለሌላው ጥሩ ምሳሌ ሆነው ሌሎች እንደእርሳቸው እንዲሠሩ ለመቀስቀስ በማለት ምን ሠሩ ? ምን አገልግሎትስ አበረከቱ ? ተብለው ሲጠየቁ ሥራዬን እግዚአብሔር ይወቅልኝ እንጂ እኔ ይህን አደረግሁ ይህን ሠራሁ ብዬ አልገልጥም ። የሠራሁትም ለእግዚአብሔርና ለወገኖቼ ስለሆነ የሚገባኝን በማድረጌ ፣ በመጽሔትና በጋዜጣ እንዲጻፍ አልፈልግም የሚሉ ውዳሴ ከንቱ የማይሹ ብዙዎች ምእመናን እንዳሉ ይታወቃል ።

ቃለመጠይቅ ሲቀርብላቸው "ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚያስተምርበት ጊዜ ሌሎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን እናንተም ለሌላው አድርጉ" በማለቱ እግዚአብሔር ያደረገልንና የሰጠንን በረከት ሁሉ ለሌላው ብናደርግ ውዳሴ ከንቱ በመሆኑ በሰው ዘንድ መመስገን ምን ጥቅም ያስገኛል ፣ በማለት ሥራቸውን ለመግለጽ ደስተኞች አይሆኑም ። ከእነዚህም መካከል ወ/ሮ ማሪያ ሊዩኒ ይገኙበታል ።

መንፈሳዊ አገልግሎት ከሚሰጡባቸው ማዕከላት አንዱ በሆነው በገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን እንድንገናኝ በስልክ ተነጋገርን ። ሰዓቱ ሲደርስ ወደቤተ ክርስቲያኑ ቅጽር ግቢ አመራሁ ቀድሜ በመድረሴ ጥቂት ጠበቅኋቸው ሰዓት አሳልፈው ስለነበረ እንደመጡ ይቅርታ ጠየቁኝና ለማኅበራዊ አገልግሎት የሚያስፈጽሙት ጉዳይ ስለነበር በዚያው ምክንያት መቆየታቸውን ገለጹልኝ ።

እኔም ማስታወሻ ደብተሬንና እስክሪብቶዬን አመቻቸሁ በትንሣኤ መጽሔት በሴቶች ዓምድ የሚያበረክቷቸውን መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎቶች ለመጻፍና ለሌሎችም ትምህርት እንደሚሆን ነገርኳቸው እሳቸው ግን በፍጹም አላደርገውም ፣ ሊሆንም አይችልም ገና ምንተሠራና ሲሉ መለሱልኝ ።

በወቅቱ ሊቀሥልጣናት ገ/ማርያም ፈለቀ የደብሩ አስተዳዳሪ በመኖራቸው እንደምንም ብለው አግባቡልኝ ከቅዱሳት መጻሕፍት ጠቅሰው በማስተማር ለሁለታችንም መንገድ ሰጡን የዚያን ጊዜ ተሳካልኝ ብዬ መጻፍ ስጀምር እንዲያው ነው ገና ምን ተሠራና ብለው ያቅማሙ ጀመር ። ያም ሆነ ይህ አልቀረም ። አንዳንድ እያሉ ዝርዝር ሁኔታውን ነገሩኝ ።

በመንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት መሳተፍ የጀመርኩት በ፲፱፻፵፯ ዓ.ም ነው የሚሉት ወ/ሮ ማሪያ ሊዮኔ በመካከለኛ ዕድሜ የሚገኙ እና ብዙ ቤተሰብ የሚያስተዳድሩ የቤት እመቤት ወ/ሮ ናቸው ። በቤተ ክርስቲያናችን ለሚከናወን የበጎ አድራጎት ሥራ ሲሏቸው ቀድመው ይገኛሉ። ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ አቅማቸው በሚፈቅደው በገንዘብ በማቴሪያልና በጉልበት ሥራ ይሳተፋሉ "መንፈሳዊ ፊልሞችን በየአድባራቱና በየገዳማቱ በማሳየት ከፍተኛ የሆነ ገቢ ለቤተ ክርስቲያን በማስገኘት በኩል የሚያደርጉት አስተዋጽኦ በቀላሉ የሚታይ አይደለም ። ከሀገርና ከዓለም አቀፍ ርዳታ ሰጪ ድርጅቶችና ከግል በጎ አድራጊዎች ጋር ተግባብቶ እርዳታ የማስመጣትና ድሆችን የመርዳት ተሰጥኦ በእጅጉ አላቸው ። ከዚህም ጋር እንግዶችን በማስተናገድ በይበልጥም ከገዳም የሚመጡ አበው መነኰሳትን በአክብሮት ተቀብለው በቤታቸው የተለየ ክፍል በመስጠት ይረዳሉ።

ከዚህም ሌላ በጠ/ላይ ቤተ ክህነት ለኀዘንም ሆነ ለደስታ ፈጥነው የሚደርሱ ናቸው ። በቅርቡ በጠ/ላይ ቤተ ክህነት ያለውን የስብከተ ወንጌል የመሰብሰቢያ አዳራሽ በአማረና በደመቀ ሁኔታ አሳድሰው መጋረጃዎች ገዝተው ለካህናትና ለምእመናን መሰብሰቢያ እንዲሆን አስረክበዋል ። በአሁኑ ጊዜ ወ/ሮ ማርያ ሊዩኒ አገልግሎት የሚሰጡባቸው ቦታዎች እጅግ ብዙዎች ቢሆኑም ከሀገርና ከዓለም ዓቀፍ ማዕከላት ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው ።

በኢ..ኦ.አ.ቤ. የምእመናን መታሰቢያ ድርጅት ለኢየሩሳሌም የሥራ አስፈጻሚ ኰሚቴ አባል ፤

— በመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር የቦርድ አባል

— በኢንተርናሽናል ሳይንስክበብ አባል

— በሐዋይ መንፈሳዊ ኰሌጅ አባል

— በገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክ.የችግረኞች መርጃ ማኅበር ፕሬዚዳንት – በደብረናዝሬት ቅዱስ ዮሴፍ ቤ.ክ የሰንበት ት/ቤት ተጠሪ–በሁለገብ መንፈሳዊ ት/ቤት ቋሚ ኰሚቴ አባል ።

በደብረ ይባቤ ቅዱስ ያሬድ ቤ.ክ· የሕንፃ ሥራ አስተባባሪ ኰሚቴ አባል ፤

—በመካነ ቅዱሳን ኢያቄም ወሐና ቤ.ክ የልማት ክፍል ኃላፊ

— በወላይታ ደብረ መንክራት አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤ.ክ የሕንፃ አሠሪ ኰሚቴ አባል ።

— በሳማ ሰንበት የቤ.ክ. እድሳትና የሕንፃ አሠሪ ኰሚቴ አባል ።

— በአሰቦት የቤ.ክ. እድሳትና የሕንፃ አሠሪ ኰሚቴ አባል ።

— በአሰቦት ደብረ ወገግ ቅድስት ሥላሴና የአቡነ ሳሙኤል ገዳም የመንገድና የቤ.ክ. እድሳት ሥራ አባል ናቸው ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ወ/ሮ ማርያ ሊዩኒ (በበዓል ዝግጅት አስተባባሪ ቋሚ ኰሚቴ አባል ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ ። እስከ መጨረሻው ድረስ በዚሁ ቀና በሆነ መልካም ሥራቸውና አገልግሎታቸው እንዲገፉበት አደራ እንላለን ።

ስለዚህም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ማንም ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ

---

ሰዓት የቆየ አልመሰለውም ።

ድራማው በ፲፩·፴ እንዳበቃ ብፁዕ አቡነ በርናባስ የድራማውን አቀራረብ አድንቀው እግዚአብሔር በኪነ ጥበቡ ሕፃናትን እየቀሰቀሰ ወላጆችን እንዲያስተምሩ ስላደረገ አመስግነው ወላጆች ልጆችን የማበረታታትና የመርዳት ግዴታ እንዳለባቸው መንፈሳዊ መመሪያ ሰጥተዋቸዋል ፤ ብፁዕነታቸው ሥራ አሠሪን የሚጠይቅ መሆኑን በማስታወስ የደብሩ አስተዳዳሪ መልአከ ኃይል አባ ኪዳነ ማርያም አየለም ያለመድከምና ያለመሰልቸት ለሰንበት ተማሮች የሚያደርጉትን ጥረትና እንክብካቤ እንዲገፉበት አደራ በማለት ጸሎት ቡራኬ አድርገው የበዓሉ ፍጻሜ ሆኗል ።

የዜናው አቅራቢ
ቄሲ· ልሣነ ወርቅ በዛብኅ





www.ethiopianorthodox.org

# በጎ አድራጊዎችን ርዳታን የሚጠይቁት ወ/ሮ ዓመተ ጽዮን

የእኔ ሕይወት እስከ
አለ ድረስ

መንፈሳዊ አገልግሎቴን አላቋርጥም የሚሉት ወ/ሮ ዓመተ ጽዮን ገብረ ዮሐንስ አሁንም በጎ አድራጊዮችን እየጠየቁ አብያተ ክርስቲያናትን በመርዳት ላይ ይገኛሉ ። በተለይ የተጀመሩ አብያተ ክርስቲያናት በቶሎ እንዲፈጸሙ



ወ/ሮ ዓመተ ጽዮን ገ/ዮሐንስ
እኒህ ናቸው

እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም "ሲል ለሰው ልጆች ምሳሌና አርአያ ሆኖ እንዲኖር አስተምሯል።

በዚህም መሠረት የጾታ ልዩነት ሳይደረግ ለተሰጠው ትምህርትና ምሳሌ ክሴቶቹ ቀዳሚውን ሥፍራ ይዘው ይገኛሉ ። ከመገልገል ይልቅ ማገልገልን ከመቀበል ይልቅ መስጠትን በመምረጣቸው ቅዱስ ቃሉን በሥራ እየተረጎሙ ይታያሉ ። ለዚህ የተቀደሰ አገልግሎታቸውም ቤ.ክ. ከጎናቸው እንደማትለይና ትብብሯን እንደማትነፍጋቸው እንተማመናለን ።

፩ኛ. አ.አ. ለሽሮ ሜዳ መንበረ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ማሠሪያ ብር ፲፩ሺ፪፻፶፰

፪ኛ. ለመካነ ቅዱሳን ኢያቄም ወሐና ብር 2552.60 ማንቲም ንዋየ ቅድሳት የሌላቸው እንዲሟላላቸው ለማድረግ የሚያደርጉት መንፈሳዊ እንቅስቃሴ እጅግ በጣም የሚያስደስት ነው ።

ከዚህ በፊት ያደረጉትን መንፈሳዊ አስተዋጽኦ እንተወውና ከ፲፱፻፹፪-፲፱፻፹፬ ድረስ ካስገኟቸው እርዳታዎች ጥቂቶቹን ቀጥለን እንመለከታቸዋለን ።

፫ኛ· ለድብረ መዳልው ኪዳነ ምሕረት ብር 2412

፬ኛ. ለዝቋላ ቤተ ክርስቲያን ብር 100 ና ግምታቸው ብር 500 የሚሆኑ ንዋያተ ቅድሳት

፭ኛ. ለግሸን ደብረ ከርቤ ግምታቸው ብር ፬፻ በላይ የሚሆኑ ዕጣንና ዘቢብ አበርክተዋል ። አሁንም ወደፊትም ከዚህ መንፈሳዊ ተግባራቸው እንዳማያቋርጡ ወ/ሮ ዓመተ ጽዮን ገብረ ዮሐንስ ተናግረዋል ፡ እኔ ይህንን መንፈሳዊ ተግባር የምሠራው ለራሴ ብቻ እጠቀማለሁ ብዬ ሳይሆን ሌሎች ምእመናን በመንፈሳዊ ስጦታቸው ከእግዚአብሔር ከፍ ያለ ክብርን ለማግኘት እንዲችሉ ለማድረግ ነው በማለት ወ/ሮ ዓመተ ጽዮን ተናግረዋል ።


በዚህ መንፈሳዊ ተግባራቸው የሰውን ፊት ሳይፈሩ ሳያፍሩ ሳይሰቀቁ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ የሚያደርጉት መንፈሳዊ ተግባር እንዲገፋበት ምኞታችን ነው ያለ ድካም ከእግዚአብሔር ዋጋን ለማግኘት አይቻልምና ።

የዜና አቅራቢ ቀ.ሊ.ልሣነ
ወርቅ በዛብኅ

# የአፈ መምህር ገበየሁ መንፈሳዊ ተግባር ።

አፈ መምህር ገበየሁ ጀንበሬ ከአሁን በፊት በጎጃም ሀገረ ስብከት በይልማና ዴንሳ አውራጃ በተለይ ከአውራጃው ርእሰ ከተማ አዴት ፲ ኪሎ ሜትር ርቆ የሚገኘውን ወነባ ቅ/ሚካኤልን ማሠራታቸው በትንሣኤ መጽሔት ታትሞ መውጣቱ ይታወሳል ።

እኒህ አባውንት አሁንም ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ሕዝበ ክርስቲያኑን በማበረታታትና በማስተባበር ከላይ ለተጠቀሰው ቤተ ክርስቲያን ከአምስት ሺህ ብር በላይ



አፈ መምህር ገበየሁ

የፊጀ ቤተ ልሔም ከ፮ሺህ (ከስድስት ሺህ) ብር በላይ የወሰዱ የካህናት ማደሪያዎች የሚሆኑ ሁለት ቤቶች ከሃያ ሺህ ብር የበለጠ የፊጀ ደጀ ሰላም አሠርተዋል ።

አፈ መምህር ገበየሁ ጀንበሬ መንፈሳዊ ተግባራቸውን በመቀጠል ጋዳ በዓታ እየተባለች የምትጠራው ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን ለብዙ ዘመን ጠፍታ ስትኖር ማኅበረ ምእመናኑን በማስተባበር ማንም ሰው የገንዘብ ርዳታ ሳያደ

# ዜና ሊቃውንት

## የመሪጌታ ወ/ሰማዕት ዓለሙ አጭር የሕይወት ታሪክ

መሪጌታ ወ/ሰማዕት ዓለሙ በወሎ ክ/ሀገር በዋድላ ደላንታ አውራጃ ልዩ ስሙ ፈንዛይት ጊዮርጊስ በተባለው ቦታ ከአባታቸው ከመምህር ዓለሙ ብሩ ከእናታቸው ከወ/ሮ ደስታ ካሣ በ፲፱፻፲፯ ዓ/ም ተወለዱ ።

ዕድሜያቸው ለትምህርት አንደደረሰ ከፊደል እስከ ቅኔ ትምህርታቸውን ከወላጅ አባታቸው ከመምህር ዓለሙ ብሩ አጠናቀው በ፲፱፻፴፩ ማዕርገ ዲቁና በዘመኑ ከነበሩት ሊቀ ጳጳሳት ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ ተቀብለዋል ።

መሪጌታ ወ/ሰማዕት ዓለሙ በዚሁ ቦታ ትምህርታቸውን በመቀጠል በደላንታ አውራጃ ዳኅና ሚካኤል ተብሎ በሚጠራው ቦታ ከመምህር ከሀሌ ገ/እግዚአብሔር ጾመ ድጓንና ምዕራፍን የተማሩ ሲሆን እንዲሁም ቀደም ሲል ከአባታቸው ሲማሩ የቆዩትን የቅኔ ትምህርት በሽድሆ ወረዳ ልዩ ስሙ ወቂጣ ማርያም በተባለች ደብር ከመምህር አወቀ በማጠናከር ለመምህርነት ብቁ ተብለው እስከሚመረጡ ድረስ ተምረዋል።

መሪ ጌታ ወ/ሰማዕት ዓለሙ በጎንደር ክፍለ ሀገር በጋይንት አውራጃ በምትገኘው ዙር አምባ ጽርሐአርያም ገዳም በቦታው እውቅ ከነበሩት የዝማሬ መዋሥዕት መምህር መጋቤ መኮንን የዝማሬ መዋሥዕት ትምህርታቸውን በብቃት ከማጠናቀቃቸውም በላይ በዚሁ ሀ/ስብከት በደብረ ታቦር አውራጃ መልዛ ሽንጌ ማርያም በተባለች ደብር በተክሌ አቋቋም በመላው ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ዝናቸው ከታወቀውና በሙያቸውም አሉ ይባሉ ከነበሩት ከመልአከ ገነት ጥሩነህ ፈለቀ ተምረዋል ።

መሪ ጌታ ወ/ሰማዕት ዓለሙ በዚህ በኋላ ምስክር ለመሆን ይችሉ ዘንድ ወደ ደብረ ታቦር ከተማ በመመለስ ደብረ ታቦር ኢየሱስ ከአለቃ ቀለመወርቅ ይማም አስፈላጊውን ሁሉ በሟሟላት በዚህ ሙያ በመምህርነት ተመርቀዋል ።

ታላቁና የዘመኑ የቤተ ክርስቲያናችን ምሳሌ መሪ ጌታ ወ/ሰማዕት ዓለሙ የተካኑበትን ሙያ በጉያቸው ሸሽገው ዛሬ ካረፉበት የመቃብር አፈር ይዘውት አልገቡም ሀገርን ወገንና ሕዝብን ይወዳሉ ያፈቅራሉ ለዚህም ነው ለቤተ ክርስቲያንና ለኢትዮጵያውያን ካላቸው ጽኑ ፍቅር የተነሳ ሙያቸውን በቤተ ክርስቲያን ለማዳረስና ተተኪ ሊቃውንትን ለማብዛት በጎጃም ክፍ/ሀገር በሞጣ አውራጃ ቀራንዮ በተባለው ታላቅ ደብር ብዙ ደቀመዛሙርቶችን አስተምረው ጥንግድርብ ካባን ቁፍጣን



መ/ወ/ሰማዕት ዓለሙ እኒህ ነበሩ

ቀሚስ ተሸልመዋል መሪጌታ ወ/ሰማዕት ዓለሙ ሞያቸው አቋቋም ማስተማር ብቻ ባለመሆኑ ቤተ ክርስቲያን የምትፈልገውንና የምትጠብቀውን ሙያ ሁሉ አስተምረዋል ።

በወሎ በአምሃራ ሣይንት አውራጃ አርባዕቱ እንስሳ በተባለ ደብር በጎንደር በደብረ ታቦር አውራጃ ሐሙስ ወንዝ ዳራ ሚካ

ርግላቸው የመቃኞ ቤተ ክርስቲያን አሠርተው ከብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የምዕራብ ጎጃም ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ በማስፈቀድ አዲሱን መቃኞ ቤተ ክርስቲያን አስባርከው የድንግል ማርያምን ጽላት እስገብተው በመቀደስ ላይ ትገኛለች ወደፊትም ዋናውን ቤተ ክርስቲያን ጥንት ከነበረበት ላይ ለማሠራት መሠረቱን በማስ ቆፈር ላይ ይገኛሉ ።

መሠረቱም በሚቆፈርበት ጊዜ ጥንት በአፈር የተዳፈኑት ንዋያተ ቅድሳት በመገኘት ላይ ናቸው ስለዚህ አሁን በመቃኞ ላይ የምትገኘውን 'ገዳ በዓታ የተባለችውን ቤተ ክርስቲያን በአዲስ ፕላን ለማሠራት በመንፈሳዊ ልቡና ደተነሡ ስለሆኑ ማንኛውም ክርስቲያን እጁን እንዲዘረጋላቸው በድንግል ማርያም ስም ይጠይቃሉ ።

የዜናው አቅራቢ
ቀ·ሊ·ኅ· ልሣነወርቅ በዛብኅ



www.ethiopianorthodox.org

ኤል በተባለ ቦታ በዚሁ አውራጃ በእስቴ ወረዳ ድንቄሳ ጊዮርጊስ ከዚያም በጋይንት አውራጃ በስማዳ ወረዳ ሳፍ ማርያም በተባለች ደብር እስከ ፲፱፻፸፪ ዓ.ም ድረስ በመዘዋወርና በማስተማር የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በማገልገል ሕያው ታሪክን ሠርተው አልፈዋል ።

መሪጌታ ወ/ሰማዕት ዓለሙ ዛሬ ለህልፈት ያበቃቸውን የሆድ ሕመም በሕክምና ለመከላከል ግንቦት ፳፭ ቀን ፲፱፻፸፪ ዓ/ም ወደ አዲስ አበባ መጥተው ሳለ የመጀመሪያው ፓትርያርክ በነበሩት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ መልካም ፈቃድ ወደ ደብረ ጽጌ ማርያም ሰኔ ፳ ቀን ፲፱፻፸፫ ዓ/ም ተመድበዋል ። ከዚያም በመቀጠል በአዲስ አበባ ከተማ በመካነ ሰማዕት ቅዱስ ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን የአቋቋምና የቅዳሴ መምህር በማስፈለጉና ለዚህ ተግባር ብቁ ችሎታ ያለው ሰው ተፈልጎ በወቅቱ የደብሩ አስተዳዳሪ የነበሩት አለቃ ሤም ከበደ መጋቢት ፩ ቀን ፲፱፻፸፫ ዓ/ም ከደብረ ጽጌ ማርያም ገዳም አስመጥተዋቸው በዚህ ደብር እንዲያስተምሩ በመምህርነት ተቀጥረዋል ።

መሪጌታ ወ/ሰማዕት ዓለሙ በዚሁ ደብር ሌት ከቀን አመመኝ ደከመኝ ሳይሉ በፍፁም ቅንነትና ግብረ ገብነት በማስተማር ብዛት ያላቸውንና ተተኪ ደቀ መዛሙርትን አፍርተዋል ።

መሪጌታ ወ/ሰማዕት ዓለሙ በተለያዩ ቦታዎች ካስተማሯቸው ደቀ መዛሙርት ለመምህርነት ደረጃ የበቁትን በምሳሌነት ለመጥቀስ ያክል ፡

፩= ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ብፁዕ አቡነ ሰላማ

፪= መሪጌታ ፈለቀ ተሰማ

፫= " ታደሰ መኮንን

፬= " ጓሉ አክሊሉ

፭= " ነቢየ ልዑል

፮= " ስብሐት

፯= " መንግሥቱ

፰= " ኤፍሬም ጌታሁን

፱= " ተሾመ ይገኙባቸዋል።

መሪጌታ ወ/ሰማዕት ዓለሙ ብሩ በዚሁ የሕይወት ዘመናቸው በጎንደር ክ/ሀገር በደብረ ታቦር አውራጃ ሐሙስ ወንዝ ወረዳ ከሕግ ባለቤታቸው ከወ/ሮ ፈንታ ነሽ ገ/ሕይወት አንዲት ሴት ልጅ ወልደዋል መሪጌታ ወ/ሰማዕት ዓለሙ ከላይ ከተጠቀሱት ሙያ ቸው ብቻ የተመረቁ ሳይሆኑ ሰው ያልወረሰውን እግዚአብሔር የሰጣቸውን ትሕትና ፍቅር ቅንነትና ትዕግስትን ፍቅረ ቢጽንን በመሳሰሉት የተመረቁ ሲሆኑ ሙያ አለኝ ብለው ሳይኮሩ ትንሽ ትልቁን እንዳከበሩ የሕይወት ዘመናቸውን ያሳለፉ የቤተ ክርስቲያን ታላቅ አባት ነበሩ ።

መሪጌታ ወ/ሰማዕት ዓለሙ በሕይወት ዘመናቸው ሲኖሩ ሰውን የማያስቀይሙና ይቅር ለእግዚአብሔር ተባብለው የማያውቁ አርአያነታቸው በታሪክ ሲወሳ የሚኖር ነው ። ሆኖም የሰው ልጅ ምንም ደግ ሥራ ቢሠራ ከሞት የሚቀር የለምና እግዚአብሔር አምላክ ለመጀመሪያው የሰው ልጅ መሬት ነህና ወደ መሬትም ትመለሳለህ ሲል ባዘዘው አምላካዊ ቃል መሠረትና ታላቁም ሐዋርያ መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ ሃይማኖቴንም ጠብቄአለሁ እሩጫዬን ሁሉ ጨርሻለሁ ወደፊት የጽድቅ አክሊል ይጠብቀኛል እንዳለው ሁሉ እነሆ በፍልውሃ ሆስፒታል በሕክምና ሲረዱ ቆይተው በተወለዱ በ፹፮ ዓመታቸው መጋቢት ፩ ቀን ፲፱፻፹፪ ዓ/ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል ።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የማትረሳቸው መሪጌታ ወ/ሰማዕት ዓለሙ ከዚህ ዓለም በሞት መለየታቸው ለ፲፱ ዓመታት ያክል ባገለገሉበት በመካነ ሰማዕት ቅ/ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን እንደተሰማ ለዚሁ ሥርዓተ ጸሎት በወጣው ፕሮግራም መሠረት ቀሳውስቱና ዲያቆናቱ በሰዓታት መዘምራኑ ደግሞ የዕለቱን ስብሐተ ነገሀ ሲያደርሱ አድረዋል ። አስከሬናቸውም ከሆስፒታሉ በሚወዷቸውና በሚያፈቅሯቸው ጓደኞቻቸው በወዳጅ ዘመድ ታጅበው መኖሪያ ቤታቸው ድረስ ፲ ደቂቃ ያክል ካረፈ በኋላ አርአያነት ባለው ሁኔታ ካህናቱ ልብሰ ተክህኖ ለብሰው ጽንሐ መስቀልና ጃንጥላ በያዙ ቀሳውስትና ዲያቆናት ጥንግ ድርብ በለበሱ መዘምራንና ከአዲስ አበባ አድባራትና ገዳማት መጥተው በሥርዓቱ ላይ በተገኙ ሊቃውንት እንዲሁም በአካባቢው ኗሪ ታጅበው ቂርቆስ አውራጃ ቀበሌ ፳፭ ከቀኑ ፬ ሰዓት ከ፴ ሲሆን ቤተ ክርስቲያን ደርሶና እስከ ቀኑ ፱ ሰዓት ድረስ ጸሎተ ፍትሐቱ ሲከናወን ውሎ የጠቅላይ ቤተ ክህነት የመምሪያ ኃላፊዎች የገዳማትና አድባራት አስተዳዳሪዎች ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶችና ብዛት ያለው የመካነ ሰማዕት ቅ/ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ካህናት እግዚአብሔር ነፍሳቸውን በወዳጆቹ በአብርሃም ይስሐቅና ያዕቆብ ዘንድ እንዲያሳርፈልን እየጸለዩን አንዲት ልጃቸውን በትምህርት ያነፃቸው የቀለም ልጆቻቸው በጣም የሚያፈቅ



ሯቸው ሊቃውንትና የቤተ ክርስቲያን ጓደኞቻቸውን ሁሉ እግዚአብሔር ያጽናችሁ እንላለን ።

<u>ስለ መምህር ወ/ሰማዕት ዓለሙ ብሩ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት ምክንያት ለመታሰቢያ የተደረሰ ቅኔ ሥላሴ ዘመልዓክ ስብሐት ተስፋ ሚካኤል መርሻ መ/ሰ/ቅ/ቂ/ቤ/አ·አ</u>

<u>ሥላሴ ቅኔ</u>

<u>ስምዖን ወልደ ሰማዕት</u> ለድንግለ ሙሴ እንተ አውሥአ
እምፃማ ዛቲ ዓለም ሕማመ አካል ያዕርፎ
ለሞት ሕፃነ ሥጋዊ በሕዕኑ ተወክፎ
ወወልደ ሰማዕት አልጸቀ ኀልቆ ሥጋሁ ጽሒፎ
ገራህተ ምልክዓምይጣተፎ
ለተክለ መድኅን አብ ዘኢያዕቀፎ
ግበ ዓይን እንተ መልሐ ሰይፎ

<u>ሥላሴ ዘሊቀ ጠበብት ምሕረቱ ጣ/ገብርኤል ደብረ ሰላም መድኃኔ ዓለም ቀጨኔ አ·አ</u>

<u>መኑመ ዘነደፎ</u> ለሐረገ ሥዕል ወ/ሰማዕት
ዘልቡስ ሥጋ ይመስል ምልዓ አካሉ ወቆሙ
ዓይነ ሞት አኮኑ ይስሕብ ቀለሙ
ያንብብዎሂ አዘዘ በመዛግብተ ጽድቅ ኩሉሙ
ዘመን ኢይጥፋዕ ትርጓሜ ስሙ
ጸሐፌ ትእዛዝ ቂርቆስ መፍቀሬ ስሙ
በእሐቲ ለንጉሥ ማሕተሙ

የመካነ ሰማዕት ቅዱስ ቂርቆስ
ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር
ጽ/ቤት

# የአዲስ አበባ ሀ/ስብከት ፩፻፶ ካህናትን አስመረቀ

በአዲስ አበባ ዋና ከተማ ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ለዘጠኝ ወራት የሠለጠኑ መቶ አምሳ ካህናት የተመረቁት መስከረም ፳፪ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ·ም ነው ።

በዚሁ ዕለት ከጧቱ ፪·፴ ደቂቃ የገዳማትና የአድባራት አስተዳዳሪዎች ጥሪ የተደረገላቸው ካህናትና ምእመናን የተመደበላቸውን ቦታ መያዝ ጀመሩ ሦስት ሰዓት ሲሆን ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ የቅዱስ ሲኖዶስ ሰብሳቢ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር በመሆን ከስብከተ ወንጌል አደራሽ ሲደርሱ የማሰልጠኛው ድሬክተር ከአሠልጣኞች መምህራንና ከሠልጣኞች ካህናት ጋር በመሆን ተቀብለዋቸዋል ።

ስብሰባው በብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ ጸሎት እንደተከፈተ መምህር ገብረ እግዚአብሔር ማዕጠንቱ ስለ ፕሮግራሙ ቅደም ተከተል ከገለጹ በኋላ የሚከተለውን ንግግር አድርገዋል ።

<u>የመ/ገብረ እግዚአብሔር ማዕጠንቱ ንግግር</u>

ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ የቅዱስ ሲኖዶስ ሰብሳቢ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት! የማሠልጠኛው መምህራን የጠ/ቤተ ክህነት የመምሪያ ኃላፊዎች የገዳማትና የአድባራት አስተዳዳሪዎች ጥሪ ተደርጎላችሁ ከዚህ ቦታ የተገኛችሁ ዕንግዶችና ትምህርታችሁን ፈጽማችሁ ለመመረቅ የመጣችሁ ካህናት እንኳን ደኅና መጣችሁ እያልኩ በአዲስ አበባ ሀ/ስብከት ካህናት ማሠልጠኛ ስም ምስጋናዋን አቀርባለሁ ካሉ በኋላ ንግግራቸውን በመቀጠል ።

<u>ብፁዕ አባታችን ሆይ! ፡</u>

ይህ ማሠልጠኛ በቅዱስ ሲኖዶስ መልካም ፈቃድና አርቆ ተመልካችነት በጥቅምት ወር ፲፱፻፹፩ ዓ·ም ተከፍቶ በየሦስት ወሩ የትምህርት ጊዜ መጨረሻ ካህናትን እያሠለጠነ ሲያስመርቅ ፬ኛ ዓመቱን የያዘ ሲሆን በ፲፱፻፹፫ ዓ·ም የዘጠኝ ወራት የትምህርት ጊዜ ከ፯ኛ ዙር እስከ 9ኛ ዙር የሠለጠኑ ፩፻፶ ካህናትን በዛሬው ዕለት ለማስመረቅ ይዞ ቀርቧል ከተጀመረ ከ፲፱፻፹፩ ዓ·ም ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ሠልጥነው የተመረቁ ካህናት ዛሬ ከሚመረቁት ጋር 450 መሆናቸው ነው ። ይህም የሚያመለክተው ቤተ ክርስቲያናችን የተማረ የሰው ኃይል በማፍራት በኩል ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ መሆኗን ነው ።

በሌላም በኩል ይህ ኮርስ ለቤተ ክርስቲያናችን ከፍተኛ ሥራ በመሥራት ላይ መሆኑን ሁሉም ሊያውቀውና ሊረዳው ይገባል ።

<u>የኮርሱ ዋና ዓላማ ፡</u>

፩ኛ ካህናት ሥራ ፈትተው በሚውሉበት ጊዜ ብዙ ንትርክና ጭቅጭቅ ይፈጠር እንደነበረ የታወቀ ነው ያ ቀርቶ ካህናቱ ወደ ዕውቀት ደረጃ እንዲያዘነብሉ በማድረግ ንትርኩና ጭቅጭቁ እየቀዘቀዘ እንዲሄድና በዚያ ፈንታ ካህናት የራሳቸውን ዕውቀት በማሻሻል ለምእመናን በቂ አገልግሎት ለማቅረብ እንዲችሉ፡

፪ኛ/ በየቀበሌውና በየሠፈሩ እየተዘዋወሩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እም



www.ethiopianorthodox.org

ነት ተከታዮች የሆኑትን ምእመ ናን ወደ አልሆነ መንገድ የሚስቡ ትን የልዩ ልዩ ሃይማኖት ሰባኪዎ ችን ለመከላከል ነው ።

፫ኛ/ የሰበኑ መንፈሳዊ ጉባኤ አስተዋጽኦ ከጊዜ ወደ ጊዜ ዕድ ገት እያሳየ እንዲሄድና የምእመና ንም መንፈሳዊ ፍላጎት እንዲሟላ ለማድረግ ሲሆን ፤

በአጠቃላይ ኮርሱ በቤተ ክህነ ትና በካህናት መካከል እንደ ታላቅ ድልድይ ሆኖ ከመገኘቱ የተነሣ አንዳንድ ችግሮች በተገ ለጹ ጊዜ በጋራ ተወያይቶ ችግሩ በቀላሉ ሊወገድ ስለሚችል ይህ ማሰልጠኛ ለቤተ ክርስቲያናችን ተጨማሪ ኃይል ነው ለማለት ይቻላል ፡

በዚህም አጋጣሚ በኮርሱ ላይ በየጊዜው እየተገኙ ሲያስተምሩ ላቆዩት ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ጠ/ቤተ ክህነት የመምሪያ ኃላፊ ዎች ሰዓቱንና ዕለቱን አክብረው በመገኘት ለኮርሰኞች ያበረከቱት ትምህርት የኮርሱ ተሳታፊዎችን በይበልጥ ዕውቀታቸውን ለማሻ ሻል እጅግ በጣም እረድቷቸዋል ። ቢባል ማጋነን አይሆንም ይህም በመሆኑ የኮርሱ ክፍለ ጊዜ ከ፫ ወደ ፮ ወር እንዲራዘም ቢደረግ የበለጠ ውጤት እንደሚያስገኝ ላሳስብ እፈልጋለሁ ።

በመጨረሻም ኮርሱ ከተጀመረ እንሥቶ ለአዲስ አበባ ሀ/ስብከ ትና ሌሎችም የሥራ ኃላፊዎች እንዲሁም ለገነተ ጽጌ ቅ/ጊዮር ጊስ አስተዳደርና ለሥራው መቃ ናት ለተባበሩን ሁሉ በመሠልጠ ኛው ስም ምስጋናዬን አቀርባለሁ በማለት የማሠልጠኛው ኃላፊ መ/ገ/እግዚአብሔር ማዕጠንቱ ንግግራቸውን አጠቃለዋል ።

ቀጥሎም ከማሰልጠኛው መም ህራን ሁለቱ ስለሥልጠና አስፈላ ጊነት ንግግር አድርገዋል ከመም ህራኑ አንዱ ሊቀ ካህናት ጥዑመ ልሣን ካሣ ሲናገሩ ሥልጠና ሰው ነትን ያፍታታል ሥልጠና እንደበ ትን ርቱዕ ያደርጋል ሥልጠና አዕ ምሮን ያሰፋል ዕውቀትን ያደረ ጃል ሥልጠና ራስን ያዘጋጃል ካሉ በኋላ ዓለም የሥልጠና ሥራ በሰው ብቻ ተወስኖ እንዲቀር አላ ደረገም የቤት እንስሳትና የዱር አራዊትም የሥልጣኔው ተካፋ ዮች እንዲሆኑ በማድረጉ ዝንጅ ሮው ሠልጥኖ መኪና ሲነዳ ስልክ ሲደውል ይታያል ብለዋል ሊቀ ካህናት ንግግራቸውን በመቀጠል ታዲያ ሥልጠና ለቤተ ክርስቲያን በይበልጥ በማስፈለጉ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙር ቱን ለስብከተ ወንጌል ወደ ዓለም የላካቸው አስተምሮ አሠልጥኖ ነው በማለት ስለ ሥልጠና ጠቃ ሚነት ሰፋ አድርገው ተናግረ ዋል።

እንዲሁም ከተመራቂዎች ካህ ናት ልብን የሚመስጡ ለዘቦች ተሰምተዋል በርከት ያሉ ቅኔዎ ችም ተነግረዋል ።

፬ኛ/ ከመምህር በላይ ዘርይሁን

ጉባኤ ቃና

ኢያመረኑ ሕሙም ጽማዌ ልበ ካህናት አዕምሮ ፤

እስመ ሥርወ ደሙ ለሰብእ ድማዌ እምድኅረ ሐመ ሠወሮ ።

ትርጓሜው

በሽተኛ ድንቁርና የካህናት ልብ አዕምሮን አላወቀምን

ድንቁርና በሽታ ልቡን ሠውሮ ታልና ።

## ዋዜማ ቅኔ

ፍሬ ጽድቅ ኢፈረየ ማዕረር ዘቃዱስ ኑፋቄ አይሁድ እሙንቱ ሦክ ድምኒ ተዋሕዶ አነቆ ለዝ ንቱ

ወፀረ ማርያም እምነ ማዕረረ ላዕሉ ወታሕቱ

እንበለ ጊዜሁ ዘየብስ ላዕለ ገራ ህቱ

ወዕመቅ ሃይማኖት አልቦቱ

ትርጓሜ

የቃዴስ አዝመራ የአይሁድ ጥርጥር የእውነት ፍሬን አላፈ ራም

የተዋሕዶ ሃይማኖት ድምፅ እሾህ አንቆ ይዞታልና ።

የእመቤታችን ድንግል ማር ያም ጠላት የላይና የታች አዝ መራ፣ ያለጊዜው ደረቀ ጥልቅ መሬት ሃይማኖት የለውምና ።

ሌሎች ፤ የአማርኛ ግጥሞችም ተነበዋል ፤ ቀጥሎም ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ሰብሳቢ ለተመራቂዎቹ የምስክር ወረቀቱን ከማደላቸውም ሌላ ከ1–3 በትምህርታቸው ብልጫ ላገኙት ካህናትም የተዘጋጀላቸ ውን ልዩ ሽልማት ሰጥተዋል ።

ቀጥሎም ብፁዕ አቡነ ናትና ኤል የአርሲ ሀ/ስብከት ሊቀ ጳጳስ መንፈሳዊ መልእክት አስተላልፈ ዋል በንግግራቸውም ላይ ተመራ ቂዎቹን እንኳን ደስ አላችሁ ካሉ በኋላ ዘመን የራሱ የሆነ መመሪያ አለው ጌታችን መድኃኒታችን ሐዋርያትን ሂዱችሁ አስተምሩ ብሎ ሲልካቸው እንደ እባብ ብል ሆች እንደርግብም የዋሆች ሆነው ማስተማር እንዳለባቸው ነግሯ ቸው ነበር እነርሱም እንደአዘዛ ቸው በመሆን መልእክታቸውን ተወጥተውታል ።

በዘመናችን ብዙ ለውጦች ተደ ርገዋል ባለፉት ዓመታት እግዚአ ብሔር የለም ተብሎ በይፋ የታወ ጁባቸው ዓመታት ነበሩ ቤተ ክር ስቲያናችን እነዚህን ዘመናት በብ ልህነት ተወጥታቸዋለች ካሉ በኋላ ብፁዕ አቡነ ናትናኤል መን ፈሳዊ መልእክታቸውን በመቀ ጠል ትምህርት ለሀገራችን ዕንግዳ አይደለም መማሩም ማስተማሩም ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አዲስ ስላይደለ ለመምህራኑም ሆነ ለሠልጣኞች ካህናት በዕው ቀት ላይ ዕውቀትን በክብር ላይ ክብርን እንደመጨመር ነው ።

መላው አፍሪካ በቅኝ አገዛዝ በነበረበት ገዜ ሀገራችን ነፃነቷ ንና ክብሯን ባሕሏን ሥርዓቷን ጠብቃ ታሪኳን መዝግባ ይዛ ለተ ከታይ ትውልድ ለማስተላለፍ የበ ቃችው በቤተ ክርስቲያናችን አማ ካይነት ነው ። በታቦት በመስቀል የቀና ሀገር አንድነቱ የጠበቀ የማ ይናወጥ ነው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ባለውለታ መሆኗ መዘ ንጋት የለበትም ብለዋል ።

በተጨማሪም ብፁዕነታቸው በእጃችን የሌለ ምንም የለም ሁሉም ከእኛው እጅ ይገኛል ከዕ ውቀታችንና ከትምህርታችን ጋር ያነጋገር ፈሊጥ ያስፈልገናል ። ይህ ማሠልጠኛ እስከዛሬ ድረስ ፬፻፶ ካህናትን ማሠልጠኑን ስን ሰማ በጣም ደስ ይለናል ።

በሥልጣኔው የተገኘውም ፍሬ አብሮ መነገር አለበት ካሉ በኋላ መልእክታቸውን ዘለግ በማድ ረግ።

ጌታችን መድኃኒታችን ሐዋር ያትን ሳያሠለጥን አልላካቸውም ሦስት ዓመት ከ፫ ወር አስተምሮ ፡ አሠልጥኖ ነው የላካቸው በ፲፬ቱም ጠቅላይ ግዛቶች ማሠል ጠኛዎች እንዲከፈቱ በቅዱስ ሲኖ ዶስ ተወስኗል በውሳኔው መሠ ረት የተከፈቱ ማሠልጠኛዎች አሉ ገና ያልተከፈቱም ይገኛሉ በማለት የሠለጠኑት ካህናት የተ ቀበሉት የምስክር ወረቀት ቢሠሩ በት የሚያስከብራቸው ባይሠሩ በት የሚያዋርዳቸው መሆኑን አሳ ስበው በትምህርታቸው ቤተ ክር ስቲያናችን እንዲያገለግሉ አደራ በማለት ብፁዕ አቡነ ናትናኤል መንፈሳዊ መልእክታቸውን አጠ ቃለዋል ።

ከዚያም በኋላ ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ የቅዱስ ሲኖዶስ ሊቀ መንበር ጸሎተ ምዕዳን አድርገው የበዓሉ ፍጻሜ ሆኗል ።

የዜና አቅራቢ ቀሲስ ልሣነ ወርቅ በዛብኅ

# የሊቀ ዲያቆናት እሸቱ ሙሴ አጭር የሕይወት ታሪክ

ሊቀ ዲያቆናት እሸቱ ሙሴ ከአባታቸው ከአቶ ሙሴ ወ ጻድ ቅና ከእናታቸው ከወ ሮ ወይርየ ለሽ አበበ በሸዋ ክፍለ ሀገር በሰ ላሌ አውራጃ በኅሀ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ደብር ነሐሴ ፳ቀን ፲፱፻፵፯ ዓ/ም ተወ ለዱ ። እድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰም በተወለዱበት ደብር ከፊደል ጀምሮ የቤተክርስቲያንን ትምህርት ሲከታተሉ ቆይተው ከዚያም ወደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም በመሄድ ግብረ ዲቁናና ሰዓታት ተምረዋል ። ከዚህም ጋር የገዳ ሙን ምግባረ ሠናይ በመከታተል በመንፈሳዊ ሕይወት ታንጸው አድገዋል ። ምክንያቱም "እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ" ተብሎ ስለተጻፈ ። ፩ኛ ጴጥ·ም·፩·ቁ·፲፮።

ከዚህ በኋላ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት የዲቁና ማዕረግ ከተቀ በሉ በኋላ በመንበረ ጸባዖት ቅድ ስት ሥላሴ ካቴድራል ከሰኔ ፲ ቀን ፲፱፻፰፰ ዓ ም ጀምሮ በዲቁና ተቀ ጥረው በወሕኒ ቤት ደብረ ምህ ረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲ ያን እየቀደሱ "ታስሬ ወደ እኔ መጥታችኋልና" የሚለውን አም ላካዊ ቃል ለመፈጸም ማቴ· ም·፳፭ ቁ· ፴፮ የሕግ እስረኞችን በማገልገልና በመንፈሳዊ ትምህር ታቸው እያጽናኑ ለተወሰነ ጊዜ ከቆዩ በኋላ በትጋትና በቅንነት የሚሰጡት መንፈሳዊ አገልግ ሎት ታይቶ በሥራ ዕድገት ወደ



ዲ እሸቱ ሙሴ እኒህ ነበሩ

ካቴድራሉ በመዛወር በዲቁና ሥራ ለብዙ ጊዜ ያገለገሉ ሲሆን ከዚህ ቀረሽ የማይባለው አገልግ ሎታቸውንና መንፈሳዊ ትጋታቸ ውን ካቴድራሉ ተመልክቶ የሊቀ ዲያቆናት ሥልጣን ተሰጥቷቸው ከቤተክርስቲያን አገልግሎታ ቸው ጋር የተከሊልና የክርስትና ክፍል ኃላፊ ሆነው ለብዙ ዓመ ታት ፍጹም የሆነ መንፈሳዊ ሥራ ቸውን በቤተ ክርስቲያንና በምዕ መናን ዘንድ በሚገባ አስመስክረ ዋል ።

በዚህም ተግባር ላይ እያሉ በመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ





www.ethiopianorthodox.org

ቤት በተዘጋጀው የካህናት ማሰልጠኛ ኮርስ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ፡ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ፡ የስብከት ዘዴ ፡ ትምህርተ አበ ነፍስ ፡ መሠረተ እምነት ፡ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንና የሥነ ጽሑፍ አቀራረብ ዘዴ የሰበካ ጉባዔያትና የሰንበት ት/ቤቶች ማጠናከሪያ ዘዴ በሚገባ ተከታትለው የምስክር ወረቀት ተቀብለዋል ።

ሊቀ ዲያቆናት እሸቴ ሙሴ በኢትዮጵያ በተለያዩ ክፍላተ አህጉር የሚገኙትን ቀደምትነት ያላቸውን ዐበይት ገዳማትን ማለትም እንደ አክሱም ጽዮን ፡ እንደ ላሊበላ ፡ ግሸን የመሳሰሉትን መንፈሳውያንና ታሪካውያን ገዳማትን በተለያዩ ጊዜያት በመዘዋወር እየተሳለሙ እየጸለዩ አምላካዊ በረከትን ሲሳተፉ የኖሩ ፍጹም የሥላሴ አገልጋይ ነበሩ ።

በዘመናዊ ትምህርት በኩልም የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በብሔራዊ ቤተ መንግሥት ት/ቤት ከተከታተሉ በኋላ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በቅድስት ሥላሴና በየካቲት ፲፪ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ፲፱፻፷፫ ዓ/ም ከማጠናቀቃቸውም በላይ በእንጦጦ አጠቃላይ የቀለምና የሙያ ትምህርት ቤት የሂሣብና መዝገብ አያያዝ ትምህርት ለ፫ ዓመታት በሚገባ ተከታትለው ፲፱፻፷፯ ዓ/ም በዲፕሎማ ተመርቀዋል ።

ከዚህም በመቀጠል ሊቀ ዲያቆናት እሸቴ ሙሴ ባላቸው ከፍተኛ የመንፈሳዊ ትምህርት ፍቅርና ቤተ ክርስቲያንንም ለማገልገል ባደረባቸው መንፈሳዊ ቅንዓት ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ የሰጡት ከፍተኛ የሆነ መንፈሳዊ አገልግሎት ታይቶ በቅዱስ ሲኖዶስና በጠቅላይ ቤተ ክህነት መልካም ፈቃድ በቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤት ለ፮ ወራት የተሰጠውን የትምህርተ መለኮት ትምህርት ተከታትለው ካጠናቀቁ በኋላ ለከፍተኛ የቴዎሎጂ ትምህርት በ፲፱፻፹፩ ዓ/ም ወደ ሶቤት ኅብረት ተልከው በሌሊንግራድ ከተማ በቴዎሎጂካል ኮሌጅ ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ እንዳሉ ባደረባቸው ሕመም ምክንያት ትምህርታቸውን አቋርጠው በዚሁ ለትምህርት በተላኩበት ሀገር በሕክምና ሲረዱ ቆይተው ሕመሙ እየፀናባቸው ስለሄደ ወደ ሀገራቸው በመመለስ በተመሳሳይ ሁኔታ ለአንድ ዓመት ከስድስት ወራት በሕክምና በፀበል ሲረዱ ቆይተው "አዳም ሆይ መሬት ነህና ወደ መሬትነትህ ትመለሳለህ" ባለው አምላካዊ ቃል መሠረት በተወለዱ በ፴፮ ዓመታቸው ነሐሴ ፴ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ/ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል ሥርዓተ ቀብራቸውም ከፍተኛና ቅን አገልግሎት በሰጡበት ቦታ "በዓለ ወልድ ቤተክርስቲያን ቅጽረ ግቢ ቤተሰቦቻቸውና መንፈሳውያን አባቶች ወንድሞችና እህቶች በተገኙበት በታላቅ ሥነ ሥርዓት ተከናውኗል ።

ሊቀ ዲያቆናት እሸቴ ሙሴ ትንሽ ትልቁን አክባሪ ፡የተጣላ አስታራቂ የተቸገረን የሚረዱ ሕሙማንን የሚጐበኙና የሕይወት ምግብ በሆነው መንፈሳዊ ትምህርታቸው የሚያጽናኑ ከዘመዶቻቸው ይልቅ ለችግረኛ አባ ትና ርኅሩኅ የሆኑ ፡ ፈጣሪ አምላካቸውን በንጹሕ ልቦና የሚያከብሩ ለሕጉና ለትእዛዙም ተገዥ ነበሩ።

የሊቀ ዲያቆናት እሸቴ ሙሴ የሕይወት ታሪክ በዝርዝር ቢጻፍ ኑሮ ጊዜና ወረቀት ባልበቃም ነበር ።

በመሆኑም የሊቀ ዲያቆናት እሸቴ ሙሴ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት ጉዳቱ ለቤተሰቦቻቸውና ለዘመድ አዝማድ ብቻ ሳይሆን ለቤተ ክርስቲያንና በቤተ ክርስቲያን ለምንገኝ መንፈሳውያን አባቶች ፡ እናቶች ፡ ወንድሞችና እኅቶች ጭምር በመሆኑ ኀዘናችን እጅግ መሪርና የፀና መሆኑን ስንገልጽ ለእናንተ ለቤተሰቦቻቸውም ቸሩ ፈጣሪያችን ብርታቱንና ጽናቱን ይስጥልን እያልን እንሰናበታችዋለን ።

ከመገበረ ወይት
አስተዳደር ጽ ቤት

## ጤናችን

# በእንስሳት ንክሻ ምክንያት የሚመጣ በሽታ

ሬበስ በእብድ እንስሳ ንክሻ ማለት በውሻ ፡ በድመት ፡ በተኩላ ወዘተ ወደ ጤናማ ሰው የሚተላለፍ አደገኛ በሽታ ነው ። ሬቤስ አልፎ አልፎ በሌሊት ወፎችና በሌሎችም እንስሳት አማካይነት በንክሻ ሊተላለፍ ይችላል ።

### የዕብድ ውሻ በሽታ መለያ ምልክቶች

፩) እንስሳው የተለየ አዲስ ጠባይ ያሳያል እንዲሁም አንገቱን ወደ መሬት ይደፋል ፡ ይቅበጠበጣል ፡ ይበሳጫል ።

፪) በአፉ አረፋ ይደፍቃል ፡ መብላት ወይም መጠጣት አይችልም

፫) አንዳንድ ጊዜ እንስሳው እንደ ዱር አውሬ ይበረግጋል ።

፬) ማንኛውንም ሰውና ሌላም በአጠገቡ የሚገኘውን ነገር ሁሉ ሳይመርጥ ይነክሳል ።

፭) የሕመም ምልክት ከታየበት ጊዜ ጀምሮ ከአሥር ቀኖች ባለበለጠ ጊዜ ውስጥ እንስሳው ይሞታል ።



# የቤተ ክርስቲያን ታሪክ

ከመ/ሉሌ መልአኩ

## የእስክንድርያ (የኮፕት) ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርኮች ስም ዝርዝር

| ተ.ቁ | የፓትርያርኮች ስም | የተሾሙበት ዓመተ ምህረት | በፓትርያርክነት ያገለገሉበት ጊዜ |
|---|---|---|---|
| 1 | ወንጌላዊው ማርቆስ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መሥራች | 61 | 7 ዓመት ከ8 ወር |
| 2 | አባ አንያኑ | 64 | 22 ዓመት ከ7 ወር |
| 3 | " ሚሊዮስ | 94 | 12 ዓመት ከ9 ወር |
| 4 | " ከርዶናስ | 108 | 10 ዓመት ከ10 ወር |
| 5 | ፕሪሙስ | 120 | 12 ዓመት ከ1 ወር |
| 6 | " ዮስቱስ | 132 | 10 ዓመት ከ10 ወር |
| 7 | " አማኒዮስ | 143 | 11 ዓመት ከ3 ወር |
| 8 | " ማሪአኑስ | 154 | 9 ዓመት ከ42 ወር |
| 9 | " ክላዲአኑስ | 163 | 14 ዓመት ከ6 ወር |
| 10 | " አግሪፒኑስ | 177 | 11 ዓመት ከ7 ወር |
| 11 | " ዩሊአኑስ | 189 | 10 ዓመት ከ1 ወር |
| 12 | " ዲሜጥሮስ ተካሌወይን | 199 | 22 ዓመት ከ7 ወር |
| 13 | " ሔራክላስ | 132 | 16 ዓመት ከ1 ወር |
| 14 | " ዲዮናሲዮስ | 149 | 19 ዓመት ከ49 ወር |
| 15 | " ማክሲሙስ | 270 | 12 ዓመት ከ47 ወር |
| 16 | " ቴስናስ | 282 | 9 ዓመት ከ49 ወር |
| 17 | " ጴጥሮስ ተፍጻሜ ሰማዕት | 293 | 10 ዓመት ከ11 ወር |
| 18 | " አቺላስ | 303 | 6 ወር |
| 19 | " አለእስክንድሮስ | 303 | 22 ዓመት ከ10 ወር |
| 20 | " አትናቴዎስ ሐዋርያዊ | 326 | 46 ዓመት |
| 21 | " ጴጥሮስ (ሁለተኛ) | 372 | 5 ዓመት ከ9 ወር |
| 22 | " ጢሞቴዎስ (አንደኛ) | 378 | 6 ዓመት ከ5 ወር |
| 23 | " ቴዎፍሎስ | 304 | 27 ዓመት ከ2 ወር |
| 24 | " ቄርሎስ ዓመደ ሃይማኖት | 412 | 31 ዓመት ከ8 ወር |
| 25 | አባ ዲዮስቆሮስ (አንደኛ) | 443 | 14 ዓመት ከ2 ወር |
| 26 | " ጢሞቴዎስ (ሁለተኛ) | 458 | 22 ዓመት ከ11 ወር |
| 27 | " ጴጥሮስ (ሦስተኛ) | 480 | 8 ዓመት ከ3 ወር |
| 28 | " አትናቴዎስ (ሁለተኛ) | 489 | 6 ዓመት ከ10 ወር |
| 29 | " ዮሐንስ (አንደኛ) | 496 | 8 ዓመት ከ7 ወር |
| 30 | " ዮሐንስ (ሁለተኛ) | 505 | 11 ዓመት |
| 31 | " ዲዮስቆሮስ (ሁለተኛ) | 516 | 2 ዓመት ከ4 ወር |
| 32 | " ጢሞቴዎስ (ሦስተኛ) | 519 | 17 ዓመት ከ4 ወር |
| 33 | " ቴዎዶሲዮስ (አንደኛ) | 536 | 31 ዓመት ከ4 ወር |

### በሰው ላይ የሚታዩ ምልክቶች

፩) በተነከሰበት የአካል ክፍል ላይ ሕመምና የመቅበጥበጥ ስሜት ይኖራል ።

፪) በጉሮሮ ሕመምና ምግብ የመዋጥ ችግር ያጋጥማል ። ወፍራም ምራቅና ልጋግ በብዛት ከአፉ ይዝረከረካል የውሃ ፍራቻ ይታይበታል ።

፫) የማንኪያ ጡንቻዎች መደንዘዝና በድን መሆን ለመዋጥ አለመቻል ።

፬) ውሃን ሲያዩ መፍራት

፭) ከባድ የራስ ምታት ሕመም

፮) ከፍ ያለ ትኩሳት

፯) ጠቅላላ የጤንነት መታወክ

፰) የሰውነት መዛል

፱) የመደንገጥ ምልክቶች መታየት ።

፲) ቅዠትና አዕምሮ መሳት በመጨረሻ ሞት ።

### የዕብድ ውሻ በሽታ ምክንያቶች

የዕብድ ዋሻ በሽታ "ሬቤስ" ኀይረስ የተባሉ ረቂቅ ሕዋሳት ናቸው ።

### የበሽታው ዕንሱ ዕለታት

ብዙ ጊዜ ከ፬—፮ ሳምንት ነው። ሆኖም እንደ ቁስሉ ከአንጐል መራቅና መቅረብ ዕንስ ዕለትም ሊረዝምና ሊያጥር ይችላል ። በዕብድ እንስሳ የተነከሰው ቁስል አንጐል አጠገብ ከሆነ የበሽታው ዕንስ ማለትም ዕለት አጭር ይሆናል ።

### የበሽታው ማኅደር

የውሻ ዘር የሆኑ የቤትና የዱር እንስሳት ናቸው ። ለምሳሌም ውሻ፣ ቀበሮ ፣ ጅብ ወዘተ ...



www.ethiopianorthodox.org

| | | | |
|---|---|---|---|
| 34 | " ጴጥሮስ (አራተኛ) | 567 | 2 ዓመት |
| 35 | " ዳሚአኖስ | 570 | 35 ዓመት ከ11 ወር |
| 36 | " አናስታሲዮስ | 606 | 12 ዓመት ከ6 ወር |
| 37 | " አንድሮኒኩስ | 619 | 6 ዓመት |
| 38 | " ቢኒአሚን (አንደኛ) | 625 | 39 ዓመት |
| 39 | " አጋሶን | 664 | 16 ሃመት ከ9 ወር |
| 40 | " ዮሐንስ (ሦስተኛ) | 681 | 8 ዓመት ከ1 ወር |
| 41 | " ይስሐቅ | 689 | 2 ዓመት ከ11 ወር |
| 42 | " ስምዖን (አንደኛ) | 692 | 7 ዓመት ከ8 ወር |
| 43 | " አለእስክንድሮስ (ሁለተኛ) | 703 | 24 ዓመት ከ9 ወር |
| 44 | " ኮዝማ (አንደኛ) | 728 | 1 ዓመት ከ4 ወር |
| 45 | " ቴዎደደሩስ | 729 | 11 ዓመት ከ7 ወር |
| 46 | " ሚካኤል (አንደኛ) | 743 | 23 ዓመት ከ6 ወር |
| 47 | " ሚና (አንደኛ) | 766 | 8 ዓመት ከ10 ወር |
| 48 | " ዮሐንስ (አራተኛ) | 776 | 22 ዓመት |
| 49 | " ማርቆስ (ሁለተኛ) | 798 | 20 ዓመት ከ3 ወር |
| 50 | " ያኮቡስ | 818 | 10 ዓመት ከ9 ወር |
| 51 | " ስምዖን (ሁለተኛ) | 829 | ከ7 ወር |
| 52 | አባ ዮሳብ (አንደኛ) | 831 | 17 ዓመት ከ11 ወር |
| 53 | " ሚካኤል (ሁለተኛ) | 849 | 1 ዓምት ከ4 ወር |
| 54 | " ኮዝማ (ሁለተኛ) | 850 | 7 ዓመት ከ7 ወር |
| 55 | " ሽኖዳ (አንደኛ) | 858 | 11 ዓመት ከ3 ወር |
| 56 | " ሚካኤል (ሦስተኛ) | 869 | 35 ዓመት ከ1 ወር |
| 57 | " ገብርኤል (አንደኛ) | 908 | 11 ዓመት |
| 58 | " ኮዝማ (ሦስተኛ) | 919 | 12 ዓመት |
| 59 | " ማካሪ (አንደኛ) | 931 | 20 ዓመት |
| 60 | " ቴዎፋኒዮስ | 951 | 4 ዓመት ከ8 ወር |
| 61 | " ሚና (ሁለተኛ) | 956 | 17 ዓመት ከ11 ወር |
| 62 | " አብራም (አንደኛ) | 976 | 3 ዓመት ከ6 ወር |
| 63 | " ፊሎቴዎስ (አንደኛ) | 979 | 24 ዓመት ከ7 ወር |
| 64 | " ዘካርያስ (አንደኛ) | 1003 | 27 ዓመት ከ11 ወር |
| 65 | " ሽኖዳ (ሁለተኛ) | 1032 | 14 ዓመት ከ7 ወር |
| 66 | " ክርስቶዱሉስ | 1047 | 22 ዓመት ከ8 ወር |
| 67 | " ቄርሎስ (ሁለተኛ) | 1078 | 15 ዓመት ከ6 ወር |
| 68 | " ሚካኤል (አራተኛ) | 1092 | 9 ዓመት ከ7 ወር |
| 69 | " ማካሪ (ሁለተኛ) | 1102 | 27 ዓመት ከ1 ወር |
| 70 | " ገብርኤል (ሁለተኛ) | 1130 | 14 ዓመት ከ3 ወር |
| 71 | " ሚካኤል (አምስተኛ) | 1144 | ከ9 ወር |
| 72 | " ዮሐንስ (አምስተኛ) | 1146 | 18 ዓመት ከ10 ወር |
| 73 | " ማርቆስ (ሦስተኛ) | 1165 | 22 ዓመት 6 ወር |
| 74 | " ዮሐንስ (ስድስተኛ) | 1188 | 26 ዓመት ከ11 ወር |
| 75 | " ቄርሎስ (ሦስተኛ) | 1234 | 7 ዓመት ከ9 ወር |
| 76 | " አትናቴዎስ (ሦስተኛ) | 1250 | 11 ዓመት ከ1 ወር |
| 77 | " ገብርኤል (ሦስተኛ) | 1269 | 2 ዓመት ከ2 ወር |
| 78 | " ዮሐንስ (ሰባተኛ) | 1271 | 23 ዓመት |

ይቀጥላል

## የበሽታው ምንጭ

ያበደው እንስሳ ለሃጭ ነው በሽታውን ለይቶ የማወቂያ ዘዴ የውሻውን አንጎል በላቦራቶሪ መመርመር ነው ።

## የበሽታው መዛመቻ መንገድ

፩) ባበደ እንስሳ በመነከስ

፪) አንዳንዴ ያበደው እንስሳ ልሃጭ በቡጭረት ዘልቆ ሲገባ

፫) የታመመ ሰው ልሃጭ ወይም ምራቅ ።

## የበሽታው የመተላለፊያ ወቅት

በውሻና በሌሎች እንስሳት የበሽታው ምልክት ከመታየቱ ከ፫ ወይም ከ፭ ቀን በፊትና እንስሳው እስኪሞት ድረስ ።

## መከላከያ

፩) ውሻውን ማሰር በየጊዜውም ማስከተብ ።

፪) ተለከስካሽ ውሾችን መግደል

፫) ከውሻው ጋር አለመላፋት ።

፬) ውሻ ወይም ድመት ያልተለመደ ጠባይ ለውጥ ሲያሳዩ ቶሎ ብሎ ማስመርመር ።

## ለበሽታው የሚጋለጡ

ደመሞቃት በሆኑ እንስሳት ሁሉ ሰውም ጭምር ነው ።

## በሽታው የሚገኝበት ቦታ

በመላው ዓለም ይገኛል። በተለይም የውሻ ቤተሰብ የሆኑ እንስሳት ከቁጥጥር ውጭ በሆኑበት ቦታና በኢትዮጵያም እጅግ ተስፋፍቶ የሚገኝ በሽታ ነው ።

## በሽታውን የመከላከያ ዘዴ

፩) በዕብድ ውሻ (እንስሳት) እንደተነከሱ ቶሎ ብሎ ክትባት

(ወደ ገጽ ፪ ዞሯል)



# ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ

የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ፡

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ ፡

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፡ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፡ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ ላላቀረቡ ግን ስምንት ብር በማስከፈል ይሰጣል ። ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የስብከተ ወንጌልና ሐዋሪያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት ፡

የስልክ ቍ·
የመልእክት ሣ·ቍ· 3137
አዲስ አበባ ፡

www.ethiopianorthodox.org